ያዕቆብ 4፡1-12

«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን? ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም። አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል። ወይስ መጽሐፍ በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅንዓት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደ ተናገረ ይመስላችኋልን? ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል፤ ስለዚህ፡- እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል። እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ። ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ ኃዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ። በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።

«ወንድሞች ሆይ፥ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ። ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም የሚፈርድ ሕግን ያማል በሕግም ይፈርዳል፤ በሕግም ብትፈርድ ፈራጅ ነህ እንጂ ሕግን አድራጊ አይደለህም። ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?»

ጦርነቶች እንዴት ያከትማሉ?

ስለ ማይጨው ጦርነት ሰምተህ ታውቃለህን? ወይም ስለ ዐድዋ ጦርነት ወይም ስለ ኮሪያ ዘመቻ ሰምተህ ታውቃለህን? እነዚህ በተለያዩ ሕዝቦች መካከል የተደረጉ ጦርነቶች ናቸው። በአብዛኛው የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ስለ እነዚህ ጦርነቶች እናነብባለን።

በሕዝቦች መካከል የሚደረጉ የተለያዩ ስምምነቶች ቢኖሩም፥ ስለ አቶሚክ ቦንብ የተደረጉ የተለያዩ ስምምነቶች ቢኖሩም፥ ጦርነት ግን የሕይወት እውነታ ነው። በሕዝቦች መካከል ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሕይወት ገጽታና የተለያዩ ደረጃዎች ጦርነት አለ። ብዙ ሱቆች ባሉባቸው መንደሮች ውስጥ እንኳ እነዚህ ፉክክሮች አሉ።

ያዕቆብ ጦርነትን ዋና ዓላማ አድርጎ በዚህ ክፍል ይናገራል። በዚህ ዓለም ላይ የሚካሄዱ ሦስት የተለያዩ ዓይነት ጦርነቶች እንዳሉ ይገልጻል። እንዴት እነዚህ ጦርነቶች መቆም እንደሚችሉም ይገልጻል።

በሰዎች መካከል የሚደረግ ጦርነት (4፡1፥ 11-12)

«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ?» በወንድሞች መካከል! «ወንድሞች በጎብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ መልካም ነው። እነሆም ያማረ ነው» (መዝ. 133፡1)። በእርግጥ ወንድሞች በፍቅርና በስምምነት መኖር አለባቸው። ብዙ ጊዜ ግን ይህ አይታይም። ሎጥ ከአጎቱ ከአብርሃም ጋር ተጣላ (ዘፍ. 13)። አቤሴሎም ከአባቱ ከዳዊት ጋር ተጣላ (2ኛ ሳሙ. 13፡18)። ደቀ መዛሙርት እንኳ በመካከላችን ታላቅ የሚሆን ማን ነው? እያሉ በመከራከራቸው ምክንያት ለጌታ ችግር ፈጥረውበት ነበር (ሉቃስ 9፡46-48)።

ከጥንት አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ የአንዳንዶቹን ስንመረምር በመካከላቸው ስምምነት እንዳልነበረ እንገነዘባለን። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በጉባኤ እርስ በእርስ ይፎካከሩ ነበር። ጉዳዮቻቸውን ወደ ፍርድ ቤት እስኪያቀርቡ ድረስ በመካከላቸው ውዝግብ ነበር (1ኛ ቆሮ. 6፡1-8 ና 14፡23-40)። የገላትያ ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው እየተበላሉና እየተነካከሱ ነበር (ገላ. 5፡15)። ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖች መንፈሳዊ አንድነታቸውን ያሳድጉ ዘንድ ለምኗቸው ነበር

(ኤፌ. 4፡1-16)። በቤተ ክርስቲያኒቱ የነበሩ ሁለት ሴቶች ተስማምተው ለመኖር ስላልቻሉና ለጳውሎስ እጅግ ተወዳጅ በነበረችው በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ተፈጥሮ ነበር (ፊልጵ. 4፡1-3)።

ያዕቆብ በቅዱሳን መካከል ስለነበሩት በርካታ የተለያዩ አለመግባባቶች አመልክቶ ነበር።

በመደብ ልዩነት ምክንያት የመጡ ጦርነቶች (2፡1-9)፡- በሀብታምና በደሀ መካከል የነበረ ለዘመናት የማያቋርጠው ልዩነትና ውድድር በዚህም እንደ ነበር እንመለከታለን። ሁልጊዜ ሀብታም ሰው ትኩረት ሲያገኝ፥ ድሀው ግን የሚመለከተው አልነበረም። ደግሞ ይናቅ ነበር። ሀብታም ይከበር ደሀው ደግሞ ይናቅ ነበር። የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለሀብታም ሰው እንክብካቤ በማድረግ ድሀውን ንቆ በመተው ወይም በመርሳት የተገላቢጦሽ የሆነ ድርጊት ሲፈጽሙ ማየት እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረግ ጎብረት እንደ ልብስና በመሳሰሉት የኢኮኖሚን ዓቅም በሚገልጹ ነገሮች ላይ የሚመሠረት ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ናት ማለት ነው።

በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ያሉ አለመግባባቶች (5፡1-6)፡- ድሀውን ሊቆጣጠረውና ሊጎዳው የሚችል ኃይል ያለው ሀብታም ሰው ነው። «ሠራተኞች ከአሠሪያቸው የሠሩበትን ዋጋ ወይም ተገቢ የሆነ ክፍያ አያገኙም ይሆናል። በዘመናችን እንደሚታየው ዓይነት የሠራተኛውን መብት የሚያስጠብቁ ናቸው የሚባሉ ማኅበራት ቢኖሩም እንኳ ጥሩ የማያገኙ ወይም ገቢያቸው ከሚሠሩት ሥራ ጋር ሲመዛዘን ፈጽሞ በቂ ያልሆነ በርካታ ሰዎች አሉ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ግጭቶች (1፡19-20፤ 3፡13-18)፡- ያዕቆብ ይህንን መልእክት የሚጽፍላቸው አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኃላፊነትና የሥልጣን ስፍራ ግጭት ወይም ጦርነት ከፍተው እንደ ነበር ደግሞ ግልጽ ነው። ብዙዎቹ አስተማሪዎች ወይም መሪዎች መሆን ፈልገው ነበር። ቃሉን በሚያጠኑበት ጊዜ ውጤቱ መንጻትና መገንባት ሳይሆን ዐመፅና ክርክር ሆኖ ነበር። እያንዳንዱ ሰው የራሱ አሳብ ብቻ ትክክል እንደሆነ፥ የራሱ መንገድ ብቻ እውነተኛውና ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ ያምን ነበር። ጉባኤዎቻቸውን መንፈሳዊ መሰጠት ሳይሆን ስግብግብነት ገዝቶአቸው ነበር።

በወንድማማቾች መካከል የነበሩ ጦርነቶች (4፡11-12)፡- ቅዱሳን አንዱ በአንዱ ላይ ክፉን ይናገር፥ ይተማማና ይፈርድ ነበር።

በዚህም ስፍራ እንደገና አንደበትን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የመጠቀምን ሁኔታ እናያለን። ክርስቲያኖች እውነትን በፍቅር ሊነጋገሩ ይገባል (ኤፌ. 4፡15)። በውድድር፥ በመቀናናትና በትችት መንፈስ ክፉ ነገሮችን ሊነጋገሩ አይገባም። ስለ አንድ ወንድም የምናውቀው እውነት ጎጂ ነገር ከሆነ በፍቅር ልንሸፍነው እንጂ ደጋግመን ልናነሣው አይገባም (1ኛ ጴጥ. 4፡8)። ኃጢአትን ካደረገ በግሉ ልናነጋግረውና ጉዳዩን ከጌታ ጋር እንዲያስተካክል ልንረዳው ይገባል (ማቴ. 18፡15-19፤ ገላ. 6፡1-2)።

ያዕቆብ መለየትን ወይም ደግሞ ሰዎችን መገምገምን አይደለም የሚከለክለን። ክርስቲያኖች የሚሻለውን ነገር ፈትነው መውደድ አለባቸው (ፊልጵ. 1፡9-10)። ነገር ግን በእግዚአብሔር ስፍራ ሆነው በሌሎች ላይ መፍረድ የለባቸውም። በመጀመሪያ እራሳችንን ልንመረምርና ቀጥሎም ሌሎችን ለመርዳት ልንጥር ያስፈልጋል (ማቴ. 7፡1-5)። በአንድ ጉዳይ ውስጥ የሚኖሩትን እውነታዎች ሙሉ በሙሉ ላናውቅ እንችላለን። በሰዎች ልብ ውስጥ ያሉትን ውስጣዊ ዓላማዎች ሁሉ እንደማናውቅ ደግሞ የተረጋገጠ ነው። በአንድ ወንድም ላይ ክፉ መናገርና በከፊል በምናውቀው መረጃና ምናልባትም ርኅራኄ በጎደለው ውስጣዊ ዓላማ በወንድም ላይ መፍረድ እርሱንም እግዚአብሔርንም መበደል ነው። ፈራጆች ለመሆን አልተጠራንም፤ ፈራጅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ ታጋሽና የሰዎችን አሳብ የሚረዳ ነው፤ ፍርዱም ጻድቅና ቅዱስ ነው፤ ስለዚህ ጉዳዩን ለእርሱ ልንተው እንችላለን።

ቅዱሳን እርስ በእርሳቸው በጦርነት ላይ መሆናቸው፥ መሪ በመሪ ላይ፥ ቤተ ክርስቲያን በሌላ ቤተ ክርስቲያን ላይ፥ ማኅበር በማኅበር ላይ መክታቸው የሚያሳዝን ነገር ነው። ዓለም እነዚህ ሃይማኖታዊ ጦርነቶች በመመልከት «እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚጣሉ ተመልከቱ» ይላል። በዚህ ምክንያት ኢየሱስ የሚከተለውን ጸሎት ጸለየ፡- «ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ . . . አንተ እንደላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም ባንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ» (ዮሐ. 17፡21)።

ታዲያ፥ እርስ በርሳችን በጦርነት የሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? የአንድ ቤተሰብ አካል ሆነን፥ አንድ አዳኝ እያመንን፥ አንዱ መንፈስ በውስጣችን አድሮ፥ እርስ በእርስ ግን እንጣላለን። ለምን? ያዕቆብ ይህንን ጥያቄ እየተካሄደ ስላለ ሌላ ሁለተኛ ጦርነት በመናገር ይመልሰዋል።

በውስጣችን የሚካሄድ ጦርነት (4፡1-3)

«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደለምን?» (ያዕ. 4፡1)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚካሄዱ ጦርነቶች ቀስቃሹ በልባችን ውስጥ የሚካሄደው ጦርነት ነው። «ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኝነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ...ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ አሉና» (ያዕ. 3፡14-16)።

የኃጢአት መሠረታዊ ይዘቱ ራስ ወዳድነት ወይም ስስታምነት ነው። ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጣሰችው የዛፍን ፍሬ በመብላት እንደ እግዚአብሔር ብልህ ለመሆን ፈልጋ ነበር። አብርሃም ሣራ ሚስቱ ሆና ሳለች እኅቴ ናት በማለት የዋሸው በራስ ወዳድነት ሕይወቱን ለማዳን ስለፈለገ ነበር (ዘፍ. 12፡10-20)። ለእስራኤል በሙሉ ሽንፈት ምክንያት የሆነውን ኃጢአትን ያደረገው ከኢያሪኮ ከተበዘበዘው ምርኮ በራስ ወዳድነት ሸሽጎ በመውሰድ ነበር (ኢያሱ 7)። «እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ» (ኢሳ. 53፡6)።

ብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ ጠቦቻችንን «በመንፈሳዊ» ሽፋን ሸፍነን እናቀርባቸዋለን። እውነቱ በሙሴ ሥልጣን ላይ መቅናታቸው ሆኖ ሳለ ስለ ሙሴ ሚስት እንዳጉረመረሙት እንደ አሮንና ማርያም ሆነን እንቀርባለን (ዘኍ. 12)። ወይም ደግሞ የሚፈልጉት እውነተኛው ነገር የክብርን ስፍራ ግግኘት ሆኖ ሳለ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ልዩ ስፍራ የፈለጉ ሆነው እንደቀረቡ እንደ ያዕቆብና ዮሐንስ እንሆናለን (ማር. 10፡35-45)። በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ የራስ ወዳድነት ውጤት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርስ ጠብና መለያየት ነው። የማርያም ኃጢአት የእስራኤል ሕዝብ የወደፊት ጉዞ ለአንድ ሳምንት ሙሉ በሙሉ እንዲቆም ምክንያት ሆኖ ነበር።

የራስ ወዳድነት ፍላጎቶች አደገኛ ነገሮች ናቸው። ወደተሳሳቱ ተግባራት ይመራሉ፤ «ትገድላላችሁ በብርቱ ትፈልጋላችሁ» (ያዕ. 4፡2)። ወደተሳሳተ ጸሎት እንኳ ሊመሩ ይችላሉ። «ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም» (ያዕ. 4፡3)። ጸሎታችን የተሳሳተ በሚሆንበት ጊዜ የክርስትና ሕይወታችን በሙሉ የተሳሳተ ይሆናል። የጸሎት ዓላማ ምን እንደሆነ በሚገባ ተነግሮአል፡-የሰው ፈቃድ በሰማይ እንዲከናወን አይደለም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንዲሆን ነው።

ከአሥርቱ ትእዛዛት የመጨረሻው «አትመኝ» የሚል ነው። ይህንን ትእዛዝ መጣስ ግን የቀሩትን ዘጠኙን እንድንጥስ ሊያደርገን ይችላል። ምኞት ሰውን እንዲገድል፥ እንዲዋሽ፥ ወላጆቹን እንዳያከብር፥ ዝሙትን እንዲያደርግ፥ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የእግዚአብሔርን የሥነ-ምግባር ሕጎች ሁሉ እንዲጥስ ሊያደርጉት ይችላል። የራስ ወዳድነት ኑሮና በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ጸሎት ሁልጊዜ ወደ ጦርነት ይመራል። በውስጥ ያለ ጦርነት በመጨረሻ በውጭ ጦርነት ወደሚደረግ መምራቱ የማይቀር ነው።

በራስ ወዳድነት ፍላጎታቸው የተነሣ ከራሳቸው ጋር በጦርነት ላይ ያሉ ሰዎች ምንጊዜም ደስተኛ አይደሉም። በሕይወት ጨርሶ ደስ አይሰኙም። ስለተቀበሉት በረከት ከማመስገን ይልቅ፥ ስላልተቀበሉት በረከት ያጉረመርማሉ። ከሌሎች ሰዎች ጋር ተስማምተው መኖር ጨርሶ አይችሉም፤ ምክንያቱም ሌሎች ሰዎች ባላቸውና በሚያደርጉት ነገር ሁልጊዜ ይቀናሉ። እውነተኛው ችግራቸው ያለው በራሳቸው ልብ ውስጥ ሆኖ እያለ ሁልጊዜ ሕይወታቸውን የሚለውጥ «አንድ ተአምራዊ» ነገርን ይፈልጋሉ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጸሎትን የእውነተኛ ፍላጎታችንን መሸፈኛ ካባ እናደርገዋለን። ክርስቲያን ሊጠቀምባቸው ከሚችሉ የስሕተት መሸፈኛዎች አንዱ «በጉዳዩ ጸልዩበት ነበር» የሚል ቃል ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በመፈለግ ፈንታ፥ እግዚአብሔር ማድረግ አለበት ብለን የምናስበውን ነገር እንነግረዋለን። ያንን ነገር ባይፈጽምልን በእርሱ ላይ መቆጣት እንጀምራለን። ይህ በእግዚአብሔር ላይ የገለጥነው ቁጣችን ከውስጣችን ሞልቶ ይወጣና በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ መቆጣት እንጀምራለን። በእግዚአብሔር ላይ ያለመታመናቸውንና መቆጣታቸውን በቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ የገለጹ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን መከፋፈልን ፈጥረዋል። ሰዎች የራሳቸውን ልብና በውስጣቸው የሚካሄደውን ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ጦርነት ቢመለከቱ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ቤተሰብ ዘንድ ያለው ችግር በተቃለለ ነበር።

እግዚአብሔር ሲፈጥረን በውስጣችን የተለያዩ ነገሮች በውሕደት አካትተን እንድንይዝ አድርጓል። በውስጣችን አእምሮ፥ ስሜትና ፈቃድ በአንድነት ይሠራሉ። ያዕቆብ በውስጣችን ከራሳችን ጋር ጦርነት ስለሚፈጠርበትና በዚህም ምክንያት እርስ በእርሳችን ስለምንፈጥረው ጦርነት በተከታታይ ይገልጻል።

ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ጦርነት(4፡4-10)

የውጫዊም ሆነ የውስጣዊ ጦርነት መሠረታዊ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዐመፅ ነው። በፍጥረት መጀመሪያ ላይ ፍጹም የሆነ የአንድነትና የስምምነት አሠራር እንመለከታለን። ኃጢአት ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ግን ግጭትን አስከተለ። ኃጢአት ሕግ የለሽ መሆኑ ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡4)፥ ሕግ የለሽነት ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ የተቃጣ ዓመፅ ነው።

አንድ አማኝ በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት የሚከፍተው እንዴት ነው? ከእግዚአብሔር ጠላቶች ጋር ጓደኝነት በማበጀት ነው። ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረን ከተፈለገ ወዳጆች እንዳናደርጋቸው ሦስት ጠላቶችን ይጠቅሳል።

ዓለም (4፡4)፡- ያዕቆብ ዓለም ሲል ከእግዚአብሔር ተለይቶ ያለው ኅብረተሰብ ማለቱ እንደሆነ እርግጥ ነው። በኅብረተሰባችን ውስጥ ያሉ የአኗኗርና የአካሄድ መንገዶች ሁሉ ፀረ ክርስቶስና ፀረ እግዚአብሔር ናቸው። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር (ያዕ. 2፡23)። ሎጥ ደግሞ የዚህ ዓለም ወዳጅ ነበር። የሎጥ መጨረሻ በሕይወቱ ውስጥ ጦርነት መከሰቱ ነበር፤ አብርሃምም ከዚህ ጦርነት ሊያድነው አስፈላጊ ሆነ (ዘፍ. 14)።

በዚህ ጥናታችን በምዕራፍ 4 እንደጠቆምኩት ክርስቲያን በዓለማዊ ጉዳዮች ተሳታፊ የሚሆነው ቀስ በቀስ ነው። በመጀመሪያ ከዚህ ዓለም ጋር ወዳጅነት ይጀምራል (ያዕ. 4፡4)። ይህም በዓለም እድፈት መበከልን ያስከትላል (ያዕ. 1፡27)። የሕይወታችን አንዳንድ ገጽታዎች የዓለም ምልክት ያረፈበትን መልክ ማሳየት ይጀምራሉ። ከዓለም ጋር የሚደረግ ወዳጅነት ዓለምን መውደድ ያስከትላል (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)። ይህም ዓለምን መምሰልን እጅግ ቀላል ያደርገዋል (ሮሜ 12፡2)። የዚህ አሳዛኝ ውጤት ነፍሳችን ከእሳት እንደሚድን ዓይነት ሆኖ (1ኛ ቆሮ. 3፡11-15) ቢድንም እንኳ ከዓለም ጋር ኩነኔን ማስከተሉ ነው (1ኛ ቆሮ. 11፡32)።

ከዓለም ጋር የሚደረግ ወዳጅነት ከአመንዝራነትጋር ተወዳድሯል። አማኝ እንደ ጋብቻ በሚቆጠር ኅብረት ከክርስቶስ ጋር ተጣምሮአል (ሮሜ 7፡4)። ስለዚህ ለክርስቶስ ታማኝ መሆን አለበት። ይህንን መልእክት የሚያነብቡ አይሁዳዊ ክርስቲያኖች «የመንፈሳዊ ምንዝርናን» ምሳሌነት እንደሚረዱ አንዳችም ጥርጥር የለውም።

ምክንያቱም የእግዚአብሔር ነቢያት የነበሩት ሕዝቅኤል፥ ኤርምያስና ሆሴዕ ይሁዳን ስለ ኃጢአቷ በሚገሥጹበት ጊዜ በዚሁ ቃል ተጠቅመውበት ነበር (ኤር. 3፡1-5፤ ሕዝቅኤል 23ና ሆሴዕ 1-2 ተመልከት)። የሌሎቹን ሕዝቦች ኃጢአት የተሞላበት መንገድ በመከተልና የአሕዛብን አማልክት በማምለክ የይሁዳ ሕዝብ በአምላኳ ላይ አመነዘረች።

ዓለም የእግዚአብሔር ጠላት ናት፤ ስለዚህ የዓለም ወዳጅ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን አይችልም። ያዕቆብ የሚጠቅሰው ሁለተኛው ጠላት ሥጋ ነው፤ ለሥጋ ፈቃድ የሚኖር ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን አይችልም።

ሥጋ (4፡1፥ 5)፡- *ሥጋ* ስንል ከአዳም የወረስነውና ለኃጢአት ምቹ የሆነው አሮጌው ተፈጥሮአችን ማለት ነው። *ሥጋ* ይህ ውጫዊ አካላችን ማለት አይደለም። *ሥጋዊ* አካላችን ገለልተኛ እንጂ ኃጢአተኛ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ውጫዊ አካላችንን እግዚአብሔርን ለማክበር ሊጠቀምበት ይችላል። አሮጌው ተፈጥሮአችን ደግሞ ውጫዊ አካላችንን ኃጢአትን ለማገልገል ሊጠቀምበት ይችላል። አንድ ኃጢአተኛ ክርስቶስን በሚቀበልበት ጊዜ በውስጡ አዲስ ተፈጥሮን ይቀበላል። አሮጌው ተፈጥሮ ግን ሊታደስም ሆነ ሊወገድ አይችልም። በዚህ ምክንያት በውስጣችን ጦርነት ይፈጥራል። «*ሥጋ* በመንፈስ ላይ መንፈስም በ*ሥጋ* ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም» (ገላ. 5፡17)። ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ሰይሞታል «በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን?...» (ያዕ. 4፡1)።

ለ*ሥጋ* መኖር ማለት በውስጣችን የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ማለት ነው። «ወይስ መጽሐፍ፡- በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅንዓት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደተናገረ ይመስላችኋልን?» (ያዕ. 4፡5)። ዓለም የእግዚአብሔር አብ ጠላት እንደሆነ ሁሉ *ሥጋም* የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጠላት ነው። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የሚኖራቸው የተቀደሰ የፍቅር ቅንዓት አለ። ይህም ተገቢና ትክክለኛ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት በቅናት ይጠብቃል። በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ኃጢአትን በምናደርግበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል።

አሮጌውን ተፈጥሮ ለማስደሰት መኖር ማለት በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት መክፈት ማለት ነው። «ስለ *ሥጋ* ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ

ጥል ነው» (ሮሜ 8:7)። ሥጋ አእምሮን እንዲቆጣጠር መፍቀድ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት በማድረግ የሚገኘውን በረከት ማጣት ማለት ነው። አብርሃም መንፈሳዊ አእምሮ ነበረው፤ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት በማድረግ ባገኘው ሰላም ደስተኛ ሆኖ ኖረ። ሎጥ ግን ሥጋዊ አእምሮ ነበረው፤ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ በሕይወቱ ጦርነት ነበር። «ለሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው» (ሮሜ 8:6)።

ሰይጣን (4:6-7):- ዓለም ከእግዚአብሔር አብ ጋር በግጭት ላይ ናት። ሥጋ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይታገላል። ሰይጣን ደግሞ የእግዚአብሔርን ልጅ ይቃወማል። ትዕቢት የሰይጣን ትልቁ ኃጢአት ነበር። ስለዚህ ከአዳኙና ከቅዱሳን ጋር በሚዋጋበት ጊዜ የሚጠቀምበት ዋና የጦር መሣሪያ ትዕቢት ነው። እግዚአብሔር ትሑቶች እንድንሆን ይፈልጋል፤ ሰይጣን ደግሞ ትዕቢተኛ ወይም ኩሩ እንድንሆን ይፈልጋል። ሰይጣን ለሔዋን ተስፋ የሰጣትና ያመነችው ነገር «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» የሚለውን ተስፋ ነበር። አዲስ ክርስቲያን በመንፈሳዊ የአመራር ስፍራ ላይ ሊቀመጥ አይገባም። «በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን» (1ኛ ጢሞ. 3:6)።

እግዚአብሔር በጸጋው እንድንታመን ይፈልጋል። ጸጋውን የበለጠ ይሰጠናል ዲያብሎስ ግን በራሳችን እንድንታመን ይፈልጋል። ሰይጣን «እራስህ ሥራው» ይለናል። እራሳችንን ከፍ አድርገን እንድንመለከትና ነገሮችን ሁሉ በራሳችን መንገድ እንድናደርግ ያበረታታናል። ስለ ሰይጣን ዕቅዶች ኢየሱስ ቢያስጠነቅቅም ጴጥሮስ በሰይጣን ወጥመድ ወደቀና ሰይፉን በመምዘዝ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሱ መንገድ ለመፈጸም ሞከረ። ያደረገው ነገር እንዴት አደገኛና ክፉ ነበር!

በአሁኑ ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያናችን ካሉት ችግሮች አንዱ በቂ አገልጋዮች ሳይኖሩ እጅግ ብዙ ባለዝናዎች መኖራቸው ነው። ክርስቲያን ሠራተኞች ከሚገባ በላይ ጎልተው በመታየታቸው ለእግዚአብሔር ክብር እጅግ አነስተኛ ቦታ ብቻ ይቀራል። ሰው ስለ ራሱ የሚመካበትና የሚኮራበት አንዳችም ነገር የለውም። በእኛ ውስጥ አንዳችም በጎ ነገር የለም (ሮሜ 7:18)። በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ የእርሱ ልጆች የሚያደርገንን «መልካም ነገር» በእኛ ውስጥ ያደርጋል (2ኛ ጢሞ. 1:6፥ 14)።

ከእግዚአብሔር ሊለዩን የሚፈልጉ ሦስት ጠላቶች፡- ዓለም፥ ሥጋና ሰይጣን ናቸው። እነዚህ ጠላቶች ከቀድሞው የኃጢአት ሕይወታችን የሚያቆጠቁጡ ናቸው (ኤፌ. 2፡1-3)። ክርስቶስ ከእነዚህ ጠላቶች ነፃ ቢያወጣንም እስካሁንም ድረስ እያጠቁን አሉ። ጥቃታቸውን ልናሸንፍ የምንችለው እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ወዳጆችና የዓለም፥ የሥጋና የሰይጣን ጠላቶች መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ከጦርነት ይልቅ በሰላም በመኖር ደስ እንድንሰኝ ያዕቆብ ሦስት ትእዛዛትን ይሰጠናል።

ለእግዚአብሔር ተገዙ (4፡7)፡- ይህ ሐረግ የወታደር ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም «በተገቢው የማዕረግ ስፍራህ ተሰለፍ» ማለት ነው። አንድ ዝቅተኛ ማዕረግ ያለው ሰው እንደ ጄኔራል እሆናለሁ ቢል ውጤቱ ችግር ነው። የተሟላ ድል ለማግኘት ዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ለአለቃ መገዛት ነው። ለእግዚአብሔር ያልሰጠነው ምንም ክፍል ቢኖር በሕይወታችን ሁልጊዜ ጦርነት ይሆናል። እራሳቸውን ያልሰጡ ክርስቲያኖች ከራሳቸውም ሆነ ከሌሎች ጋር መኖር የማይችሉት ለዚህ ነው።

ጳውሎስ በኤፌ. 4፡27 ላይ ሲያስጠነቅቅ «ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት» ብሎአል። ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት በእኛ ሕይወት ውስጥ መረማመጃን ይፈልጋል፤ እኛም ያንን መረማመጃ እንሰጠዋለን። ሰይጣንን የምንቃወምበት መንገድ እራሳችንን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ነው።

ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ካመነዘረና ባሏን ከገደለ በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል ኃጢአቱን ደበቀ። በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል ጦርነት እንደነበረ ዳዊት ተናግሯል። መዝሙረ ዳዊት 32 ና 51ን በማንበብ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር በጦርነት በማሳለፉ የከፈለውን ከፍተኛ ዋጋ መመልከት ይቻላል። በመጨረሻ ዳዊት ራሱን ለእግዚአብሔር ባስገዛ ጊዜ ሰላምና ደስታን አገኘ። ይህንኑም በመዝሙር 32 እና በመዝሙር 51 ላይ ይገልጸዋል። እራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት በፈቃድ የሚፈጸም ተግባር ነው። «የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቅድ ይሁን» ማለት ነው።

ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ (4፡8)፡- ይህንን የምናደርገው እንዴት ነው? ኃጢአታችንን በመናዘዝና እንዲያነጻን በመጠየቅ ነው። «እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብ ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።» አንጹ ተብሎ በዚህ ስፍራ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ስለ ቅድስና አካሄድ የሚናገር ነው። ይህ በቁጥር 4 ላይ

የተጠቀሰውን «የመንፈሳዊ ምንዝርናን» አሳብ በማነፃፀር የሚያቀርብ ነው።

ዶክተር ኤ. ደብሊው. ቶዘር ከመጻሕፍቶቻቸው በአንዱ ላይ «መቅረብ መምሰል ነው» (*Nearness is Likeness*) በሚል ርእስ ሰፊ ጽሑፍ ጽፈዋል። እግዚአብሔርን በመምሰል እያደግን በሄድን ቁጥር ለእግዚአብሔር ቅርብ እየሆንን እንሄዳለን። እኔ በሳሎን ውስጥ ከድመቴ ጋር ቁጭ ብልና ባለቤቴ ግን ያለችው 7 ሜትር ርቃ በኩሽና ውስጥ ቢሆንም ቅርበቴ ከድመቷ ይልቅ ለባለቤቴ ነው። ምክንያቱም ድመቷ እኔን የምትመስልበት አንዳችም ነገር የለም። በጣም ጥቂት የጋራ የሆነ ነገር ብቻ ነው ያለን።

እግዚአብሔር ከእኛ እንዲርቅ የሚያደርገውን በሕይወታችን ያለውን ኃጢአት በምናስወግድበት ጊዜ በጸጋው ወደ እኛ ይቀርባል። እኛን ከሌላ ከማንም ጋር ሊጋራ አይሻም። በእኛ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ሊኖረው ይገባል። በሁለት አሳብ የሚወላውል ክርስቲያን ጨርሶ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ አይችልም። እንደገና አብርሃምና ሎጥን ልናስታውስ እንችላለን። አብርሃም ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ስለ ሰዶም ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ (ዘፍ. 18፡23-33)። ሎጥ ግን ወደ ሰዶም በመግባት የእግዚአብሔርን በረከት ሁሉ አጣ።

በጌታ ፊት ራስን ማዋረድ (4፡9-10)፡- በውጫዊ ገጽታ እራስን ለእግዚአብሔር ያስገዙ መስለው በውስጥ ግን እራስን በትሕትና ዝቅ ሳያደርጉ መኖር ይቻላል። እግዚአብሔር የትዕቢትን ኃጢአት ይጠላል (ምሳሌ 6፡16-17)። ስለዚህ ትዕቢት የነፋው አማኝ ትሑት እስኪሆን ድረስ በተገቢ የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ያስተምረዋል። ኃጢአትን እንደ ቀልድ የማየት እንዲያውም በኃጢአት ላይ የማፌዝ ዝንባሌ ይታይብናል (ሳቃችን ወደ ኃዘን ሊለወጥ ይገባዋል)። ኃጢአት እጅግ ክፉ ነገር ስለሆነ የእውነተኛ ትሕትና አንዱ ምልክት የኃጢአትን አደገኝነት ተገንዝቦ አለመታዘዝን ለማስወገድ ጥረቱን በሚገባ መያዝ ነው። «የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» (መዝ. 51፡17)።

አንዳንድ ጊዜ አማኝ «እግዚአብሔር ሆይ ትሑት አድርገኝ» የሚል ጸሎት ሲጸልይ ይሰማል። እንደዚህ ዓይነት ጸሎት መጸለይ አደገኛ ነገር ነው። እራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ትሑት አድርገን ኃጢአታችንን በመናዘዝ በኃጢአታችን እጅግ በማዘን እርግፍ አድርገን ብንተወው ይሻላል። «ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ»

(ኢሳ. 66:2)። «እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፥ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል» (መዝ. 34:18)።

እነዚህን ሦስት ትእዛዛት ብንከተል እግዚአብሔር ወደ እኛ ይቀርባል፤ ያነጻናል፤ ይቅርም ይለናል፤ ጦርነቶቹም ያቆማሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ካለን ከራሳችንና ከሌሎችም ጋር ሰላም ይኖረናል። «የጽድቅም ሥራ ሰላም፥ የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል» (ኢሳ. 32:17)።

የሕይወትህን አስተዳደር በእግዚአብሔር ትከሻዎች ላይ ተውና እርሱ የሰላም ልዑል ይሁንልህ (ኢሳ. 9:6)።

ያዕቆብ 4፡13-17

«አሁንም፡- ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን፤ በዚያም ዓመት እንኖራለን፤ እንነግድማለን፤ እናተርፍማለን፤ የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና። በዚህ ፈንታ፡- ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል። አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመጣላችሁ፤ እንደዚህ ያለ ትምክሕት ሁሉ ክፉ ነው። እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።»

አስቀድመህ ዐቅድ

ያዕቆብ ምዕራፍ 4ን ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚደረግ ጦርነት በመናገር ይጀምርና ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ በመግለጽ ይደመድመዋል። እነዚህ ሁለት ዋና አሳቦች የተያያዙ ናቸው። አንድ አማኝ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ችግር ፈጣሪ እንጂ ሰላምን አድራጊ ሊሆን አይችልም።

ሎጥ ወደ ሰዶም በመግባት ለቤተሰቡ ችግርን አስከተለ። ዳዊት የአመንዝራነትን ኃጢአት በመፈጸሙ ወደ ቤተሰቡና ወደ መንግሥቱ ችግርን አመጣ። ዮናስ እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ ምክንያት በርካታ ተጓዦች የነበሩበትን መርከብ ከነጭነቱ በውኃ ውስጥ እንዲቀበሩ ሊያደርግ ምንም አልቀረውም ነበር። በእነዚህ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ እጅግ የተሳሳተ ዝንባሌ ነበር።

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ሕይወት የራሱ የሆነ ዕቅድ እንዳለው የማያሻማ እውነት ነው። እርሱ የጥበብ አምላክ ስለሆነ ምን መፈጸም እንዳለበትና ይህም መቼ እንደሚፈጸም አስረግጦ ያውቃል። የፍቅር አምላክ ስለሆነ ለልጆቹ የሚያስበው ከሁሉም የተሻለውን ነገር ነው። ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፈቃድ የፍቅሩ ጸጋ መግለጫ እንደሆነ ከመመልከት ይልቅ፥ የግድ መወሰድ እንዳለበት መራራ መድኃኒት አድርገው ይቆጥሩታል።

አንድ ጊዜ በወጣቶች ኮንፍራንስ ላይ አንድ ልጅ ወደ እኔ መጥቶ፡- «ሕይወቴን ለጌታ መስጠት እወድ ነበር ግን እፈራለሁ» አለ።

«የምትፈራው ምንድን ነው?» ብዬ ጠየቅሁት።

«እግዚአብሔር አደገኛ ነገር እንዳደርግ ይጠይቀኛል ብዬ እፈራለሁ!» ብሎ መለሰልኝ።

«አደገኛ ሕይወት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ያለ ሕይወት አይደለም፤ አደገኛ ሕይወት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ነው» ብዬ መለስኩለት። በዓለም ላይ ለሕይወትህ ዋስትና ያለው ስፍራ ቢኖር እግዚአብሔር እንድትሆንበት የሚፈልገው ስፍራ ነው።

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅ በአገልግሎቴ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፍ ነበር። በዕረፍት በነበርኩበት ስፍራ እግዚአብሔር አንዳንድ ማረጋገጫዎችንና ግበረታቻዎችን እንዲሰጠኝ በመጠየቅ የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍን አነብብ ነበር። ለዚህ ጸሎቴ መልስ የሆነኝ መልእክት በመዝ. 33:11 ላይ:- «የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል፥ የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው።» የሚለው ነበር።

«የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ልብ ነው። ስለዚህ የእርሱ ፈቃድ የፍቅሩ መግለጫ ነውና ልፈራ አይገባም» ብዬ ለራሴ ተናገርኩ። ይህ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመውደድና በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የመኖርን በረከት ለማወቅ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረስኩበት ጊዜ ነበር።

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ ላይ ሰዎች ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሊኖራቸው ስለሚችለው ሦስት ዝንባሌዎች ይናገራል። ከእነዚህ ሦስት ዝንባሌዎች እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊያዳብረው የሚገባው ትክክለኛው ዝንባሌ አንድ ብቻ ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቸል ማለት (4:13-14፥ 16)

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ ላይ የሚናገረው በጉባኤው ውስጥ ስላሉ ሀብታም ነጋዴዎች ሳይሆን አይቀርም። ስለ ንግድ እንቅስቃሴአቸው በመነጋገር ስለ ወደፊት ዕቅዳቸው በትምክሕት እየተናገሩ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለመፈለጋቸውና ስለ ውሳኔዎቻቸው መጸለያቸውን የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም። በሕይወት ውስጥ የተገኘ ስኬታማነትን የሚመዝኑት ምን ያህል ጊዜ በራሳቸው ዕቅድ እንደሄዱና ያወጡት ዕቅድ ምን ያህል ግቡን እንደመታ በመመዘን ነበር።

ያዕቆብ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከመፈለግ ቸል ማለት እንዴት ዓይነት ሞኝነት እንደሆነ ለማስረዳት አራት ጠንካራ አሳቦችን ያቀርባል።

የሕይወትን ውስብስብነት (4:13):- ሕይወት የሚያካትታቸውን ነገሮች አስብ። ዛሬ፥ ነገ፥ መግዛት፥ መሸጥ፥ ማትረፍ፥ መክሰር፥ ወደዚህና ወደዚያ መሄድ ወ.ዘ.ተ. ሕይወት በሕዝብ፥ በስፍራ፥ በተለያዩ ተግባራትና ግቦች በቀናትና በዓመታት የተሠራ ነው። አብዛኛዎቻችን በርካታ ጠንካራ ውሳኔዎችን ከዕለት ወደ ዕለት እናደርጋለን።

ሕይወት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከተለየ ከሰው መረዳት በላይ ምሥጢር ይሆናል። ሕይወት ስሜት የሚሰጥና ትርጉም ያለው የሆነልህ

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ ባወቅህበትና ፈቃዱን ለማድረግ በወሰንክበት ጊዜ ነው። በዙሪያህ ያለው ቁሳዊ ዓለም እንኳ አዲስ ትርጉም ይሰጥህ ጀመረ። በሕይወትህ በዋስትና መራመድንና በጎ አመለካከትን ያበጀኸውም ከዚያ በኋላ ነበር። የምትኖረው ምሥጢራዊና ሥጋት በሞላበት ዓለም መሆኑ አከትሟል። «ይህ የሰማያዊው አባቴ ዓለም ነው» ብለህ ለመዘመር ትችላለህ።

የሕይወትህ እርግጠኛ አለመሆን (4፡14)፡- ይህ ሐረግ የተመሠረተው በምሳሌ 27፡1 ላይ ነው። «ቀን የሚያመጣውን ምን እንደሆነ አታውቅምና ነገ በሚሆነው አትመካ።» እነዚህ የንግድ ሰዎች በሚቀጥለው ቀን ምን እንደሚሆን እንኳ ሳያውቁ ለዓመቱ በሙሉ የሚሆን ዕቅድ ያወጣሉ። ምን ያህል የእርግጠኝነት ስሜት ይሰማቸው እንደነበር ከተጠቀሙበት ንግግር ተመልከት፡- «ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን፤ በዚያም ዓመት እንኖራለን፤ እንነግድማለን፤ እናተርፍማለን።»

ዝንባሌያቸው በሉቃስ 12፡16-21 ታሪኩ የተጠቀሰውን ገበሬ ያስታውሰናል። ይህ ሰው እጅግ ፍሬያማ የሆነ እርሻ ነበረው፤ የሚያከማችበት ጎተራ ግን አነስተኛ ስለ ነበር የተሻለ ትልቅ ጎተራ በማሠራትና በማከማቸት ወደፊት ያለ አንዳች ሥጋት ለመኖር ወሰነ። «ነፍሴንም፡- አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ» አለ (ቁጥር 19)።

ለዚህ ሰው የትምክሕት ንግግር የእግዚአብሔር መልስ ምን ነበር? «አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤» (ቁጥር 20) የሚል ነበር። ሕይወት እርግጠኝነቱን የሚያጣው ለእኛ እንጂ ለእግዚአብሔር አይደለም። እርሱ እንደሚመራን ስለምናውቅ በፈቃዱ በምንሆንበት ጊዜ ብቻ ስለ ነገ እርግጠኞች እንሆናለን።

የሕይወት አጭር መሆን (4፡14)፡- ቅዱሳት መጻሕፍት እጅግ በተደጋጋሚ ከሚናገሩአቸው ዋና ዋና አሳቦች አንዱ ይህ ነው። ሕይወትን በዓመታት ስንለካው ረዥም ይመስለናል። ከዘለዓለም ጋር በሚወዳደርበት ጊዜ ግን ሕይወት እንደ እንፋሎት ነው። ያዕቆብ ይህንን ሥዕላዊ መግለጫ ያገኘው ስለ ሕይወት አጭርነት በርካታ ሥዕላዊ መግለጫዎች ከሚገኝበት ከመጽሐፈ ኢዮብ ነው።

«ዘመኔ ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ ይቸኩላል፥ ያለ ተስፋም ያልቃል» (ኢዮብ 7፡6)። «ደመና ተበትኖ እንደሚጠፋ፥»

(ኢዮብ 7፡9)። «ዘመናችን በምድር ላይ እንደ ጥላ ነውና» (ኢዮብ 8፡9)። «ዘመኔ ከሚሮጥ ሰው ይልቅ ይፈጥናል» (ኢዮብ 9፡25)። ተልእኮአቸውን ለማድረግ ስለሚቸኩሉ ንጉሣውያን መልእክተኞች የሚከተለውን ነገር ጽፈዋል፦ «የደንገል ታንኳ እንደሚፈጥን ንስርም ወደ ንጥቂያው እንደሚበርር ያልፋል» (ኢዮብ 9፡26)። «ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ነው፥ መከራም ይሞላዋል። እንደ አበባ ይወጣል፥ ይረግፋልም፥ እንደ ጥላም ይሸሻል፥ እርሱም አይጸናም» (ኢዮብ 14፡1-2)።

በየልደት ቀናችን የኖርንባቸውን ዓመታት እንቆጥራለን። እግዚአብሔር ግን የኖርንባቸውን ዓመታት ሳይሆን ቀናት እንድንቆጥር ይፈልጋል (መዝ. 90፡12)። በጊዜ ውስጥ የምንኖረው ቀናትን ነው፤ ዕድሜያችን እየገፋ በሄደ ቁጥር እነዚያ ቀናት በፍጥነት ያልፋሉ።

ሕይወት በጣም አጭር ስለሆነ እንደፈለግን አናባክነውም፤ ደግሞም የሕይወት ዘመናችንን ማባከንም አንፈልግም። ሕይወታችንን ዘላለማዊ በሆኑ ነገሮች ማሳለፍ አለብን።

እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጠው በቃሉ ውስጥ ቢሆንም ብዙ ሰዎች ግን መጽሐፍ ቅዱስን ቸል ይላሉ። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለየትኛውም የሕይወት ገጽታችን የሚሆኑ ግንዛቤ ልናገኝባቸው የሚያስፈልጉ ነገሮችን፥ መመሪያዎችንና የተስፋ ቃሎችን ሰጥቶናል። የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና መታዘዝ በሕይወት ስኬታማነትን የማግኛ እርግጠኛ መንገድ ነው (ኢያሱ 1፡8 እና መዝ. 1፡3)።

የሰው ደካማነት (4፡16)፡- «አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፤ እንደዚህ ያለ ትምክሕት ሁሉ ክፉ ነው።» የሰው ትምክሕት ድካሙን ለመሸፈን የሚደረግ ጥረት ብቻ ነው። ታምስ ኢኬምፕስ ሲጽፍ «ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈጽማል» አለ። ሰለሞን አስቀድሞ «ዕጣ በጉያ ይጣላል መደብዋ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው» ብሏል (ምሳሌ 16፡33)። ሰው ወደፊት የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ለመቆጣጠር አይችልም። የወደፊትን የማየት ጥበብም ሆነ የወደፊቱን የመቆጣጠር ችሎታ የለውም። ስለዚህ መመካቱ እራሱን አምላክ ማድረጉ ነውና ኃጢአት ነው።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቸል ማለታቸው ከፍተኛ ሞኝነት ነው። ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ያለ ካርታ፥ ወይም ማዕበል በሚያጠቃው ባሕር ያለ ኮምፓስ (አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ) እንደመሄድ ነው።

በአሜሪካ ውስጥ ኬንቱኪ በተባለችው ክፍለ አገር የምትገኘውን የማመትን ዋሻ ስንጎበኝ መውጫና መግቢያው በማይታወቀው በተራራው ውስጥ በተፈለፈለው የዋሻ መንገድና በውስጡ የሚበራው መብራት በሚጠፋበት ጊዜ በተፈጠረው ድቅድቅ ጨለማ ተደንቄያለሁ። «የመድረክ ድንጋይ» ተብሎ የሚታወቀው ስፍራ ላይ ስንደርስ የዚያ ስፍራ ኃላፊ «ከመሪያችሁ አትራቁ» የሚል ሁለት ቃል ያለው ስብከት ሰብኮናል። በእርግጥ መልካም ምክር ነበር ብዬዋለሁ።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ ያለመታዘዝ (4፡17)

በዚህ ክፍል የሚመደቡ ሰዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያወቁ ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። ይህ ከመጀመሪያው በላቀ ሁኔታ ትምክሕት የሞላበት ዝንባሌ ነው። ምክንያቱም የዚህ ዓይነት ሰው እግዚአብሔርን እንዲህ ይለዋል፡- «ምን ላደርግ እንደምትፈልግ አውቃለሁ፥ ነገር ግን ያለማድረግን እመርጣለሁ። ስለዚህ ጉዳይ አንተ ከምታውቀው የበለጠ በእርግጥ አውቃለሁ!» «አውቀዋት ከተሰጣቸው ከቅድስት ትእዛዝ ከሚመለሱ የጽድቅን መንገድ ባላወቋት በተሻላቸው ነበር» (2ኛ ጴጥ. 2፡21)።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያወቁ የማይታዘዙት ለምንድነው? ቀደም ብዬ አንዱን ምክንያት ጠቅሻለሁ፡- ይኸውም ትምክሕት ነው። ሰው የወደፊት ዕድሉን የሚወስን የነፍሱ ጌታ እራሱ እንደሆነ በመቁጠር መመካትን ይወዳል። ሰው ማንኛውንም ነገር ለማድረግ እንደሚችል አድርጎ እራሱን እንዲቆጥር የሚያሳስበውን በርካታ ድንቅ ውጤቶችን አስመዝግቧል።

ሌላው ምክንያት ደግሞ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከሁሉ በላይ መሆኑ ያለማወቁ ነው። የሰው ልጅ አኗኗር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቢፈልግ ሊያደርግ፥ ባይፈልግ ደግሞ ሊተው እንደሚችል አድርጎ የሚቆጥር መሆኑን የሚያሳይ ነው። እውነታውን ስንመለከት ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አማራጭ ሳይሆን ግዴታ ነው። «ብንፈልግ ልንቀበለው ባንፈልግ ደግሞ ልንተወው» የምንችል ነገር አይደለም። እርሱ ፈጣሪ ሆኖ እኛ ፍጡሮቹ ስለሆንን ልንታዘዘው ግዴታችን ነው። እርሱ አዳኝና ጌታ ሲሆን እኛ ደግሞ ልጆቹና አገልጋዮቹ ነንና ልንታዘዘው ግዴታችን ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደ ቀልድ መውሰድ የእግዚአብሔርን ቅጣት ወደ ሕይወታችን መጋበዝ ነው።

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ሕይወትን ለጉስቁልና የሚዳርግ ነው የሚል የተሳሳተ አሳብ አላቸው። እውነታው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ሕይወትን ለጉስቁልና አሳልፎ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ አለመታዘዝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስና የሰው ልጆች ታሪክ የዚህ ምስክሮች ናቸው። አንድ ታዛዥ ያልሆነ ክርስቲያን በዚህ ምድር ሕይወቱ ከችግሮች ለማምለጥ ቢችል እንኳ ጌታን በሚገናኝበት ጊዜ ምን ሊመልስ ይችላል? «የጌታውንም ፈቃድ አውቆ ያልተዘጋጀ እንደፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል፤ ያላወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል» (ሉቃስ 12፡47-48)።

ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያወቁ ያልታዘዙ ክርስቲያኖች ምን ይሆናሉ? የሚወዳቸው አባታቸው ፈቃዳቸውን ለፈቃዱ እስኪያስገዛ ድረስ ይቀጣቸዋል (ዕብ. 12፡5-11)። እራሱን አማኝ እያለ የሚጠራ ክርስቲያን በጌታ ካልተገሠጸና ካልተቀጣ አስቀድሞም እውነተኛ ዳግም ልደትን እንዳልተለማመደ ይህ ማስረጃ ነው። ዳግም ልደትን የሚመስል ነገር እንጂ እውነተኛውን ዳግም ልደት አላገኘም። የእግዚአብሔር ተግሣጽና ቅጣት የፍቅሩ እንጂ የጥላቻው መግለጫ አይደለም። ምድራዊ አባቶች የሆንን እኛ ፈቃዳችንን እንዲያከብሩና እንዲታዘዙን ልጆቻችንን እንደምንቀጣቸው ሁሉ ሰማያዊ አባታችንም የራሱ የሆነውን ልጆቹን ይቀጣናል። ቅጣትን መቀበል ቀላል ባይሆንም በውስጡ እጅግ አጽናኝና አበረታች የሆነ የልጅነት እውነትን ይዞአል።

ሰማያዊ የሆኑ ሽልማቶችን የማጣት አደጋም አለ። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 9፡24-27 አማኝን በግሪኮች የእሽቅድድም ውድድሮች ውስጥ ከሚካፈል ሯጭ ጋር ያወዳድረዋል። በውድድሩ ውስጥ የተዘጋጀውን ሜዳይያ ለመሸለም የውድድሩን ሕጎች ማክበር አለበት። ሕጎቹን የሚጥስ አንዳችም ነገር ቢገኝበት በውርደት ከውድድሩ ይሰረዛል። በ1ኛ ቆሮ. 9፡27 ላይ የሚገኘው «የተጣልሁ እንዳልሆን» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደኅንነትን ስለ ማጣት አይደለም፤ ነገር ግን ሽልማትን ስለማጣት ነው። ከውድድር «መውጣት ወይም መታገድ» ለዚህ አሳብ የሚስማማ በጣም ጥሩ ሐረግ ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያለመታዘዝ አሁን ቀላል ነገር ቢመስልም ጌታ በሚመለስበትና ሥራችንን በሚመረመርበት ጊዜ ግን እጅግ ከባድ ችግር ያስከትላል (ቆላ. 3፡22-25)።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝ (4፡15)

«እግዚአብሔር ቢፈቅድ» የሚለው ቃል አንድ አማኝ በከንፈሮቹ የሚናገረው ቃል ብቻ ሳይሆን የማያቋርጥ የልብ ዝንባሌ መሆን አለበት። ኢየሱስ «የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው» ብሎ ነበር (ዮሐ. 4፡34)። ጳውሎስ ስለነበረው ዕቅድ ለወዳጆቹ ሲያካፍል ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ በተደጋጋሚ ይናገር ነበር (ሮሜ 1፡10፤ 15፡32፤ 1ኛ ቆሮ. 4፡19፤ 16፡7)። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያይ የነበረው ጠፍሮ አስሮ እንደያዘው እንደ ሰንሰለት ሳይሆን የነፃነትን በሮችን ከፍቶ ነፃ እንደሚያወጣው ቁልፍ ነበር።

በዚህ ዓለም ያሉ ነገሮች ሁሉ የሚሠሩት በተለያዩ ሕጎች ነው። ከእነዚህ ሕጎች ጋር በመተባበር እየጠበቅናቸውና እየታዘዝናቸው ብንሄድ ዓለም ከእኛ ጋር ይሠራል። እነዚህን ሕጎች ብንዋጋቸውና አንታዘዝም ብንል ዓለም በእኛ ላይ ይነግሳል። ለምሳሌ፡- ለመብረር የሚያስችሉ አንዳንድ ሕጎች አሉ። የአውሮፕላን ሥራ በሚነደፍበትና በሚገነባበት ጊዜ መሐንዲሱ ለእነዚህ ሕጎች ተገዥ ነው። እንዲሁም አውሮፕላን አብራሪው እነዚህን ሕጎች በመፈጸም ይህ ትልቅ ሰው ሠራሽ በራሪ አካል በሚገባ ሲሠራ በማየት የሚገኘውን ደስታ ይካፈላል። ለመብረር የሚያስችሉትን መሠረታዊ ሕጎችን ሳይታዘዙ ቢቀሩ ግን ውጤቱ ግጭት፥ የገንዘብና የሕይወት መጥፋት ይሆናል።

እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለው ፈቃድ ለእኛ ተለይቶ የተዘጋጀ ሲሆን በዓለም ውስጥ እንዲሠሩ ያበጃቸው ሕጎች ግን አጠቃላይ ናቸው። ከዚህ በስተቀር እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ እንዲሠለጥኑ ያበጃቸው ሕጎችና እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ሕይወት ያለው ዕቅድ ሊነፃፀሩ ይችላሉ። ሙሉ በሙሉ በአንድ ዓይነት ዕቅድ የሚመሩ ሁለት ሕይወቶች ሊኖሩ አይችሉም።

በእርግጥ ለክርስቲያኖች ሁሉ የጋራ የሆኑ ነገሮች አሉ። እራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንድንሰጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ ለሁላችንም እውነት ነው (2ኛ ቆሮ. 8፡5)። ከፍትወተ-ሥጋ ኃጢአት (የሥነ-ምግባር ጉድለት) እንርቅ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (1ኛ ተሰ. 4፡3)። ክርስቲያኖች ሁሉ በጌታ ደስ እንዲላቸው፥ እንዲጸልዩና እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (1ኛ ተሰ. 5፡16-18)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ አማኞችን የሚመለከቱ ትእዛዛት በሙሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ አካል ስለሆኑ እንጠብቃቸው

ዘንድ ያስፈልጋል። ነገር ግን በሕይወታችን ዘመን ውስጥ ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ዓይነት ሥራዎች እንድንሠራ ወይም በተመሳሳይ ስጦታዎችና አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያንን እንድናገለግል የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ልብስ ሠፊ ለተለያዩ ሰዎች በተለያየ መጠን በልካቸው እንደሚያዘጋጀው ዓይነት እግዚአብሔርም ለእያንዳንዳችን ያለው ፈቃድም ይለያያል።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ ትክክለኛ የሆነ ዝንባሌ እንዲኖረን እጅግ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሕይወት የለሽና ባለቤቱ ከባድ ማሽን (ሞተር) ጋር አመሳስለውታል። ስለሆነም ሞተሩን እንዲሠራ እግዚአብሔር አስጀምሮታል (ለኩሶታል)። ሥራውን ያለማቋረጥ በሚገባ እንዲሠራ ግን ኃላፊነቱ የሰው ድርሻ ነው። በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ካልታዘዝን ማሽኑ እንዳይሠራ ስለምናደርገው በቀሪው ዘመናችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እንሆናለን ይላሉ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ሕይወት የለሽና በድን ማሽን አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በአንዳንድ ቴክኒክ እንደሚሠራ ማሽን ልንወስነው አንችልም። የእግዚአብሔር ፈቃድ በእግዚአብሔርና በአማኙ መካከል የሚኖር ሕያው ግንኙነት ነው። ይህ ግንኙነት አማኙ በማይታዘዝበት ጊዜ ወዲያውኑ የሚቋረጥ አይደለም። ምክንያቱም አባት ልጅን በሚያጠፋበት ጊዜ ይቀጣዋል እንጂ አይተወውም።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደ ሕይወት የለሽና በድን ማሽን ከማየት ይልቅ የሚያድግ ሕያው አካል አድርጎ መመልከትን እመርጣለሁ። በሰውነቴ ውስጥ አንድ ነገር በሚገባም መሥራቱንም ሲያቆም ወዲያውኑ አልሞትም። ይህ የታወከው የሰውነቴ ክፍል እንደገና በትክክል መሥራት እስኪጀምር ሌሎች የሰውነት ክፍሎቼ የእርሱን ተግባር ለማገዝና ለመርዳት ይሞክራሉ። ሕመምና ድካም ሊኖር ቢችልም ሞት ግን ወዲያውኑ ላይከሰት ይችላል።

እኔና እናንተ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ስንወጣ ወዲያውኑ የሁሉም ነገር ፍጻሜ ይሆናል ማለት አይደለም። በተለያየ ችግር ውስጥ እንደምንሆን የታወቀ ነው፤ በፈቃደኝነት እግዚአብሔር የማይገዛን ከሆነ፥ እኛ ከተገዛንላቸው ነገሮች በላይ መሆን ይገዛናል። የአንድን አካል ችግር ሌሎች የሰውነት ክፍሎቻችን እንደሚያካክሱት ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ወደ ራሱ መልሶን ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ይህንንም ከአብርሃምና ከዮናስ ሕይወት በምሳሌነት ተመልክተናል።

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ያለው የአማኝ ግንኙነት የሚያድግ ልምምድ ነው። በመጀመሪያ ፈቃዱ ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን (የሐዋ. 22፡14)። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ አስቸጋሪ አይደለም። ለመታዘዝ ፈቃደኞች እስከሆንን ድረስ ፈቃዱን ሊገልጥልን ፍጹም ፈቃደኛ ነው (ዮሐ. 7፡17)። «መታዘዝ የመንፈሳዊ እውቀት አካል ነው» ተብሎ የተጠቀሰው አባባል እውነት ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱን ለተጠራጣሪና ለግድየለሽ ሰው አይገልጥም። ለተዘጋጁና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ለሆኑ ወገኖች ግን ጌታ ፈቃዱን ይገልጣል።

ነገር ግን ጥቂቶቹን የእግዚአብሔር ፈቃድ በማወቅ ብቻ መወሰን የለብንም። እግዚአብሔር የሚፈልገው የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላብን ነው (ቆላ.1፡9)። በአንዳንድ ጉዳዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈለግና በሌሎች ቸል ማለት ትክክል አይደለም። በሕይወታችን ውስጥ ያሉ ነገሮች በሙሉ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ዝርዝር ነገር የራሱ ዕቅድ አለው።

እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድንረዳ ይፈልጋል (ኤፌ. 5፡17)። መንፈሳዊ ጥበብ የሚመጣው በዚህ መንገድ ነው። አንድ ትንሽ ልጅ የአባቱ ፈቃድ ምን እንደሆነ ሊያውቅና ምክንያቱን ግን ላይረዳ ይችላል። አንድ ትንሽ ልጅ የነገሩን «ምንነት» ሊረዳ ቢችልም ለምን እንደዚያ እንደሆነ ግን አይረዳም። እኛ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ «ወዳጆች» በመሆናችን እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ለምን እንደሚያደርግ የመረዳት መብት አለን (ዮሐ. 15፡15)። «ለሙሴ መንገዱን አስታወቀ ለእስራኤል ልጆችም አደራረጉን» (መዝ. 103፡7)። እስራኤላውያን እግዚአብሔር ምን እያደረገ እንደነበረ ያውቁ ነበር። ሙሴ ግን እግዚአብሔር ያንን ነገር ለምን እንዳደረገ ያውቅ ነበር።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልንፈትነው ወይም ትክክለኛነቱን ልናረጋገጥ ደግሞ ይገባል (ሮሜ 12፡2)። የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጉም «በልምምድ ማረጋገጥ» ማለት ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ በመኖር በእርግጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ማረጋገጥ አለብን። ታዛዦች እየሆንን በሄድን ቁጥር እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን ነገር ለማወቅ ቀላል ይሆንልናል። ይህ መዋኘትንና የሙዚቃ መሣሪያ መጫወትን እንደመማር ነው። ብዙ ልምምድ ካደረግህ በኋላ የምታደርገውን ነገር ምን እንደሆነ አጥርቶ የማወቅ ስሜት ይሰማህና ሁለተኛ ተፈጥሮህ ይሆናል።

«እግዚአብሔር ለሕይወቴ ያለውን ዕቅድ እንዴት ለማወቅ እችላለሁ?» የሚለውን ጥያቄ ያለማቋረጥ የሚጠይቁ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ጨርሶ ሞክረው እንደማያውቁ መግለጣቸው ነው። ማድረግ እንዳለብህ ከምታውቀው ነገር ጀምሮ ያንን አድርገው፤ ቀጥሎ እግዚአብሔር ለሚቀጥለው እርምጃ የሚሆነውን ነገር ይገለጥልሃል። በልምድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ በመፈተን ታውቃለህ፤ ታረጋግጣለህም። ስኬታማ ከመሆንም ካለመሆንም እንማራለን። «ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ ...» (ማቴ. 11:29)። ቀንበር የሚያመለክተው ነገሮችን በአንድነት ማቀናጀትንና እግዚአብሔር ያስተማረንን የማድረግ ጉዳይ ነው።

በመጨረሻው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልባችን ማድረግ አለብን (ኤፌ. 6:6)። ዮናስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቅ ነበር። ከተቀጣም በኋላ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጓል። ያደረገው ግን ከልቡ አልነበረም። ዮናስ ምዕራፍ 4 የሚያመለክተው ይህ ቁጡ ነቢይ ጌታንም ሆነ የነነዌ ሕዝቦችን እንደማይወድ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያደረገው ከሌላ ተጨማሪ ቅጣት ለማምለጥ ብቻ ብሎ ነበር።

ጳውሎስ ስለ መስጠት የተናገረው ነገር ለሕይወት አኗኗርም ልንጠቀምበት እንችላለን። «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና ... በኃዘን ወይም በግድ አይደለም» (2ኛ ቆሮ. 9:7)። በኃዘን ማለት «እያመነታ ደስ ሳይሰኝ» ማለት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በማድረጋችሁ አንዳችን ደስታ አታገኙም። በግድ ማለት ደግሞ ያለ አንዳች ውዴታ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የሚታዘዙት ፈልገው ሳይሆን መታዘዝ ስላለባቸው ነው። ልባቸው ከድርጊቱ ጋር አይደለም።

የደስተኛ ሕይወት ምሥጢር በመታዘዝ ደስ መሰኘት ነው። አንድ ተግባር በደስታ ሲፈጸም ሸክሞች በረከቶች ይሆናሉ። «በእንግድነቴ አገር ሥርዓትህ መዝሙር ሆነችኝ» (መዝ. *[119]:54*)። እግዚአብሔርን በምንወድበት ጊዜ የእርሱ ሥርዓቶች መዝሙሮቻችን ይሆናሉ፤ በደስታ እግዚአብሔርን እናገለግላለን። እግዚአብሔር በኃዘን፥ ወይም ማድረግ ስላለብን ብቻ ተገድደን ስናገለግለው ሥራውን ልንፈጽም እንችላለን፥ እኛ ግን በረከቱን እናጣለን። አገልግሎት ሳይሆን ጥረት ወይም ድካም ይሆንብናል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልባችን በምናደርግበት ጊዜ ግን ሥራው ምንም ያህል ከባድና አስቸጋሪ ይሁን እንባረካለን።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅም ሆነ በማድረግ አንዳንድ ጊዜ ስኬታማ ያለመሆን ከጌታ ጋር ያለንን ግንኙነት ይጎዳዋል ብለን ጨርሶ

ልናስብ አይገባም። ኃጢአታችንን በመናዘዝ ይቅርታን ከእግዚአብሔር ዘንድ ልንቀበል እንችላለን (1ኛ ዮሐ. 1፡9)። ከስሕተቶቻችን ለመማር እንችላለን። ዋናውና አስፈላጊው ነገር እግዚአብሔርን የሚወድና ፈቃዱን ለማድረግና ስሙን ለማክበር በእርግጥ የሚፈልግ ልብ ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ የሚገኙ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው? በመጀመሪያ ደረጃ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሚደረግ ጥልቅ ኅብረት ሐሤትን ታደርጋለህ (ማር. 3፡35)። የእግዚአብሔርን እውነት የማወቅና (ዮሐ. 7፡17) የጸሎትህን መልስ የማየት (1ኛ ዮሐ. 5፡14-15) መብት ይኖርሃል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሰው ሕይወትና ተግባር ዘላለማዊ ጥራት ወይም ብቃት ይኖራቸዋል (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ሽልማት የማግኘት ተስፋ እንደሚኖርም የተረጋገጠ ነው (ማቴ. 25፡34)።

ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሊኖራቸው ይችላል ብለን ከላይ ከተመለከትናቸው ሦስት ዝንባሌዎች መካከል ለእግዚአብሔር ፈቃድ አንተ ያለህ ዝንባሌ የትኛው ነው? ዕለታዊ ዕቅድህንና ውሳኔዎችን በምታደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በቸልታ ትተዋለህን? ወይስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያወቅክ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሳትሆን ትቀራለህ? እነዚህ ዝንባሌዎች የተሳሳቱና በሰው ሕይወትም ኃዘንና ጉዳትን ብቻ የሚያመጡ ናቸው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቅ፥ የሚወድና የሚታዘዝ ክርስቲያን ግን በዚህ ምክንያት በሚያገኛቸው በረከቶች ደስተኛ ሆኖ ይኖራል። የሚያራምደው ሕይወት ቀላል ባይሆንም የተቀደሰና ደስተኛ ኑሮ ግን ይኖራል። ምግቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ይሆናል (ዮሐ. 4፡34)። የልቡ ደስታና ሐሤትም ይህ ይሆናል (መዝ. 40፡8)።

ያዕ. 5፡1-6

«አሁንም እናንተ ባለ ጠጎች፥ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ። ሀብታችሁ ተበላሽቶአል፥ ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል። ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል፥ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል። ለኋለኛው ቀን መዝገብን አከማችታችኋል። እነሆ፥ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፥ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባኦት ጆሮ ገብቶአል። በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል በሴሰኝነትም ኖራችኋል፤ ለእርድ ቀን እንደሚወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል። ጻድቁን ኮንናችሁታል ገድላችሁትማል፤ እናንተን አይታወምም።»

ገንዘብ ይናገራል

አንድ ታዋቂ የኪነ ጥበብ ሰው እንዲህ አለ፡- «ገንዘብ የሚናገር ከሆነ በዘመኔ ሁሉ የሚለኝ ነገር ቢኖር ደኅና ሰንብት» ነው።

ያዕቆብ በዚህኛው ክፍል ለሚናገራቸው ሰዎች ግን ገንዘብ «ደኅና ሁኑ» አላላቸውም። እነዚህ ሰዎች ሀብታም ነበሩ። ሀብታቸው ግን ማሰናከያቸው ነበር። ሀብታቸውን ለግል የስኬታምነት ፈቃዳቸው ብቻ በመጠቀም ድሆችን ያጎሳቁሉ ነበር።

ያዕቆብ በምዕራፍ 5 ውስጥ ከሚናገርባቸው ዋና ዋና አሳቦች አንዱ ችግር ነው። የድካማቸውን ዋጋ የተከለከሉ ድሆችን እናያለን (5፡4)። በሥጋቸው የታመሙ (5፡13-16)ና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ወደ ኋላ የተመለሱ ሰዎችንም እንመለከታለን (5፡19-20)። ያዕቆብ የሚናገርበት ሁለተኛው ዋና አሳብ ደግሞ ጸሎት ነው። የድካማቸውን ዋጋ የተከለከሉ ሠራተኞች ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ (5፡4)። መከራን የሚቀበሉና የታመሙ ሰዎች መጸለይ አለባቸው (5፡13-16)። በጸሎት ከሚያምኑ ሰዎች ኤልያስን በምሳሌነት ይጠቅሳል(5፡17-18)።

እነዚህን ሁለት ዋና ዋና አሳቦች በምናገኝበት ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ክርስቲያን ከሚታወቅባቸው ምልክቶች አምስተኛ ወደሆነው ነገር እንደርሳለን። በሳል ክርስቲያን በተለያዩ ችግሮች ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ በጸሎት ይተጋል። ችግር በሚመጣበት ጊዜ ተስፋ ቆርጦ ለችግሩ እጁን ከመስጠት ይልቅ ይህ የበሰለ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር በጸሎት በመቅረብ ከእርሱ ዘንድ መለኮታዊ እርዳታ ይሻል። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያልበሰለ ሰው በራሱ ልምምድና ችሎታ ይታመናል፤ ወይም እርዳታን ከሌሎች ዘንድ ይሻል። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ የሚያስፈልገንን ነገር በሌሎች ሰዎች በኩል እንደሚሰጠን የታወቀ ቢሆንም ይህ ስጦታ ወይም የምናገኘው ድጋፍ የጸሎት ውጤት መሆን አለበት።

ያዕቆብ ሀብታም መሆን ኃጢአት ነው አላለም። ለምሳሌ አብርሃም ሀብታም ሰው ነበር። አካሄዱን ግን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ። እግዚአብሔርም አብርሃምን ለዓለም ሁሉ ለሚደርስ በረከት ተጠቀመበት። ያዕቆብ ግን ያተኮረው በሀብታም ሰዎች ስስት ላይ ነው።

«ዋይ ዋይ እያሉ እንዲያለቅሱ» ይመክራቸዋል። ለዚህ ምክሩ ምክንያት የሚሆኑ ሦስት ነጥቦችን አቅርቦአል።

ሀብታቸውን ያገኙበት መንገድ (5:4-6)

መጽሐፍ ቅዱስ ሀብት ማግኘትን አይቃወምም። በሙሴ ሕግ ሀብትን ስለማግኘትና ስለመጠበቅ የተጻፉ ግልጽ የሆኑ ሕጎች ይገኛሉ። በከነዓን የሚገኙ አይሁዶች የራሳቸው የሆነ ንብረት ነበራቸው። በዚህ ንብረታቸው በመሥራት ከፍሬው ተጠቃሚ ሆነዋል። ኢየሱስ ለማስተማር በተጠቀመባቸው በርካታ ምሳሌዎች ለግል ንብረትና ሀብት ያለውን ቀና አመለካከት ገልጾአል። በመልእክቶቹ ውስጥ የ ግል ሀብት መያዝንና ማፍራትን የሚቃወም አንዳችም ነገር አናገኝም።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሚኮንነው ነገር ሀብትን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሕጋዊ ላልሆኑ ዓላማዎች ማካበትን ነው። ነቢዩ አሞጽ ሀብታሞች የሆኑ ድሆችን በመዝረፍ ያገኙትን ገንዘብ እጅግ ስስታምነት ለሞላበት ዓላማ የሚጠቀሙ የገዥው ክፍል አባላትን የሚመለከት የፍርድ መልእክት አመጣ። ኢሳይያስና ኤርምያስ በተጨማሪ የሀብታሞችን ስግብግብነት በማጋለጥ ፍርድ በደጅ እንደሆነ በማሳየት አስጠንቅቀዋል። ያዕቆብ የጻፈበትም መንፈስ ይህ ነው። ሀብታሞች ሀብታቸውን ስላካበቱበት መንገድ ሁለት መግለጫዎች ይሰጣል።

የሠራተኞችን የድካም ዋጋ በመከልከል (5:4):- ሠራተኞች የድካማቸውን ዋጋ የሚያገኙት በየቀኑ ስለ ነበር ምንም ሕጋዊ ውል አልነበራቸውም። በማቴ. 20:1-16 ላይ የተጠቀሱት ሠራተኞች ምሳሌ በዚያን ዘመን ስለነበረው አሠራር አንዳንድ ነገሮችን ይጠቁመናል። በድካማቸው ዋጋ የሚኖሩ ሠራተኞች ጨቋኝ ከሆነ አሠሪ ይጠበቁ ዘንድ እግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ትእዛዝን በሕግ ውስጥ አስፍሮአል።

«ደሀና ችግረኛ የሆነውን ምንደኛ፥ ከወንድሞችህ ወይም በምድርህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚቀመጡት መጻተኞች ቢሆን፥ አታስጨንቀው። ድሀ ነውና ነፍሱም ጠንክራ ትፈልገዋለችና ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮኽብህ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በቀኑ ስጠው» (ዘዳግ. 24:14-15)።

«በባልንጀራህ ግፍ አታድርግ፥ አትቀማውም። የሞያተኛው ዋጋ እስከ ነገ ድረስ በአንተ ዘንድ አይደርብህ» (ዘሌዋ. 19:13)።

«ቤቱን በግፍ ሰገነቱንም በዓመፅ ለሚሠራ፥ ባልንጀራውንም እንዲያው በከንቱ ለሚያሠራ፥ ዋጋውንም ለማይሰጠው ... ወዮለት» (ኤር. 22፡13)።

እነዚህ ሀብታሞች የተለያዩ ሠራተኞችን የተወሰነ ዋጋ ለመክፈል እየተስማሙ ይቀጥሯቸዋል። ሠራተኞቹ የተሰጣቸውን ሥራ በጊዜው ቢያጠናቅቁም የድካማቸውን ዋጋ ግን አይከፍሏቸውም። አዲስ ኪዳን በመጀመሪያ በተጻፈበት በግሪኩ ቋንቋ «ተይዞበት» ተብሎ በአማርኛ የተተረጎመው ቃል ሠራተኞቹ ደመወዛቸውን ጨርሶ አግኝተው እንደማያውቁ ይገልጻል።

«አትስረቅ» የሚለው ቃል ልንታዘዘው የሚገባ ሕግ እንደመሆኑ መጠን አሁንም ቢሆን የእግዚአብሔር ሕግ ነው። እንደ ክርስቲያን ማንኛውንም ክፍያ በታማኝነት መክፈል እንዳለብን የሚያመለክት ነው። አንድ መጋቢ የማያምኑ ሰዎች ለክርስቲያኖች ገንዘብ እንዳበደሩና ክርስቲያኖቹም የተበደሩትን ለመክፈል ፈቃደኞች እንዳልሆኑ ሲነግረኝ እጅግ አፈርሁ።

በሆስፒታል ሰው ለመጠየቅ ሄጄ በነበርኩበት ጊዜ ሐኪም የሆነ ጓደኛዬን አገኘሁት። «ነገሮች ሁሉ እንዴት ናቸው?» ብዬ ጠየቅኩት እርሱም ሲመልስ «ነገሮች ሁሉ መልካም ይመስሉኛል» አለ። ላበረታታው ብዬ «እጸልይልሃለሁ» አልኩት።

እርሱም መልሶ «አመሰግንሃለሁ፤ ደስ ይለኛል! ስትጸልይልኝ ግን ገንዘብ ለተበደሩኝ ሰዎችም ሁሉ ጸልይ። ገንዘቡን በወቅቱ ቢከፍሉኝ በጣም ደስ ይለኝ ነበር!» አለኝ።

ፍርድ ቤቶችን መቆጣጠር (5፡6)፡- ብዙ ጊዜ ሀብት ያላቸው ሁሉ የፖለቲካ ኃይልም ይኖራቸዋል። ስለዚህ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ያገኛሉ። ያዕቆብ «እናንተ ግን ድሆችን አዋረዳችሁ። ባለጠጎቹ የሚያስጨንቋችሁ አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤትም የሚጎትቱአችሁ እነርሱ አይደሉምን?» በማለት ጠይቆአል (ያዕቆ ብ 2፡6)።

ወተርጌት የሚለው ስም ሲነሣ ማንም ሰው ቢሆን፡- አንድ ውብ ሆቴል ነው ብሎ የሚያስብ የለም። ይህ ቃል በአሜሪካን ታሪክ ውስጥ የተፈጸመ የሐሰት ቅሌትን በማጋለጥ የፕሬዝዳንቱን ከሥልጣን መውረድ ያስከተለ አስጸያፊ ድርጊት ነው። አንዱ ክፍል ሌላውን ክፍል ሕግን ያለ አግባብ በመጠቀምና ፍርድን አጣምሞአል በማለት ይከሰዋል።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሕዝብ አድርጎ ሲያቆማቸው የፍርድ አሰጣጥ መንገድን አዘጋጅቶላቸው ነበር (ዘዳ. 17:8-13 አንብብ)። ዳኞች ስለታም እንዳይሆኑ አስጠንቅቆአቸዋል (ዘጸ. 18:21)። ለሀብታምም ሆነ ለደሀ ማዳላት አልነበረባቸውም (ዘሌ. 19:15)። ማንኛውም ዳኛ በሐሰት መስካሪ ላይ መፍረድ አለበት (ዘዳ. 19:16-21)። ጉቦኝነት በጌታ ተኮንኖአል (ኢሳ. 33:15፤ ሚክ. 3:11፤ 7:3)። ነቢዩ አሞጽ በጊዜው በነበሩ ጉቦን በሚቀበሉና ፍርድ በሚያጣምሙ ዳኞች ላይ የፍርድን ቃል አሰምቶ ነበር (አሞጽ 5:12፥15)።

በያዕቆብ ዘመን የነበሩ የፍርድ ማስከበሪያ ተቋማት በቂ ገንዘብ ያለው ሰው በቀላሉ የሚቆጣጠራቸው ዓይነት ነበሩ። ድሆች ሠራተኞች ውድ የሆኑ የሕግ ጠበቃዎችን ለማቆም ስለማይቻላቸው ሁልጊዜ ይጠቁ ነበር። ሠራተኞች ቅን ፍርድ የሚጠይቅ ጉዳይ ቢኖራቸውም ቅን ፍርድ ግን አይሰጣቸውም ነበር። በዚያ ፈንታ ያለ አግባብ ይበዘበዙና ይጎዱ ነበር። (በዚህ ቦታ የተጻፈው መግደል የሚለው ቃል በያዕ. 4:2 እንዳለው ሥዕላዊ መግለጫ ሳይሆን አይቀርም። በእርግጥ ሀብታሞች ድሆችን እስከ ሞት ድረስ እየጨቆኗቸው ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።) ድሆች ሊዋጉ የሚችሉበት መሣሪያ ስላልነበራቸው ሀብታሞችን ለመቋቋም አይችሉም ነበር። ድሆች ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ቅን ፍርድ ወደሚሰጣቸው አምላካቸው መጮኽ ብቻ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሀብትን እንዳናካብት ያስጠነቅቀናል። ሀብት ሁሉ የእግዚአብሔር ነው (መዝ. 50:10)። ለእርሱ ሀብት ባለ አደራ እንሆን ዘንድ በክብር ተመርጠናል። «በችኮላ የምትከማች ሀብት ትጎድላለች፤ ጥቂት በጥቂት የተከማቸች ግን ትበዛለች» (ምሳሌ 13:11)። «የትጉ እጅ ግን ባለጠጋ ታደርጋለች» (ምሳሌ 10:4)። «ባለጠጋ ለመሆን አትድከም» (ምሳሌ 23:4)። በሕይወታችን ተቀዳሚውን ስፍራ መያዝ ያለበት እግዚአብሔር ነው። ይህን ስናደርግ እርሱ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ሁልጊዜ ይሰጠናል (ማቴ. 6:33)።

ሀብታሞች ሀብታቸውን የሚጠቀሙበት መንገድ (5:3-5)

በጎጢአት ሀብትን ማግኘት እጅግ ክፉ ነገር ነው። ያንን ሀብት ጎጢአት በተሞላበት መንገድ መጠቀም ደግሞ የባሰ ክፉ ያደርገዋል።

ያከማቹታል (5፡3)፡- ገንዘብን መቆጠብና ማጠራቀም በራሱ ኃጢአት አይደለም። «ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና» (2ኛ ቆሮ. 12፡14)። «ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው» (1ኛ ጢሞ. 5፡8)። «ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፍ ጋር እወስደው ነበር» (ማቴ. 25፡27)።

የሠራተኞችን የድካም ዋጋ ሳይከፍሉ ገንዘብን ማጠራቀም ግን ስሕተት ነው። እነዚህ ሀብታሞች እህል፤ ወርቅንና ልብስን ያከማቹ ነበር። እነዚህ ንብረቶች ስላሏቸው ሀብታም የሆኑ መስሎአቸው ነበር። ሀብታቸውን ለእግዚአብሔር ክብር በማዋል በሰማይ መዝገብን ከማከማቸት ይልቅ (ማቴ. 6፡19-34) ለራሳቸው ጥበቃ፥ ምቾትና ደስታ በስስታምነት መንፈስ እያጠራቀሙት ነበር። ያዕቆብ ይህንን መልእክት ከጻፈ አሥር ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ ወደቀችና የተጠራቀመው ሀብት በሙሉ የሌሎች ሆነ።

ኢየሱስ «ንብረታችሁን በሰማይ አከማቹ» ሲል ምን ማለቱ ነበር? ለወጣቱ ሀብታም ሰው እንዳለው ንብረታችንን ሁሉ ሸጠን ለድሆች ማከፋፈል አለብን ማለት ነውን? አይመስለኝም። ኢየሱስ ለሀብታሙ ወጣት እንደዚያ ያለው ስግብግብነት ወይም ሁሉንም መመኘት የሀብታሙ ሰው ገዥ ኃጢአቱ ስለነበረና ይህንንም ለመግለጥ ስለፈለገ ነው። በሰማይ ንብረትን ማከማቸት ማለት ያለንን ነገር ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ንብረት ባለ አደራ ሆነን መጠቀም ማለት ነው። እኔና እናንተ በርካታ ንብረቶች ሊኖሩን ይችላሉ። የነዚያ ንብረቶች ባለቤት ግን አይደለንም። የነገሮች ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው፤ እኛ ደግሞ አደራ ጠባቂዎች ነን።

እንደ ራሳችን ንብረት አድርገን የምንጠቀምባቸው ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ናቸው። ለፈቃዱ እራሳችንን ስናስገዛና የሰጠንን ሁሉ እርሱን ለማገልገል ስንጠቀምበት እነዚያ ነገሮች ለዘለዓለም ይጠቅሙናል። በምድር የምናደርገው ሁሉ በሰማይ ይመዘገባል፤ እግዚአብሔር የዚያ መዝገብ ጠባቂ ስለሆነ ወለዳችንን ይከፍለናል።

ሰዎች በሰማይ ንብረትን ከማከማቸት ይልቅ ለመጦሪያቸው ንብረትን ሲያጠራቅሙ ማየት የሚያሳዝን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቁጠባንም ሆነ ትርፍ በሚያስገኝ ተግባር ላይ ገንዘብን ማዋልን

አይቃወምም፤ ገንዘብን ለግል ጥቅም ብቻ ለማዋል በምሥጢር ማካበትን ግን ይኮንናል።

ሌሎች እንዳይጠቀሙ ያደርጋሉ (5፡4)፡- ሀብታሞች ድሆችን ይዘርፋሉ ማለት ነው። እነዚህ ሀብታሞች ይጠቀሙ የነበረው የራሳቸውን ሀብት ሳይሆን ለሠራተኞቻቸው ሊከፈል በሚገባ ሀብት ነበር። ምናልባትም የሠራተኞቻቸውን ደመወዝ ይቀንሱ ነበር ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ባለ አደራዎች እስከሆንን ድረስ እርሱ የሰጠን የተለያዩ ኃላፊነቶች አሉብን። ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ነገር ለሌሎች ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀምበት ይገባል። «እንደዚህም ሲሆን፥ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል» (1ኛ ቆሮ. 4፡2)። ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ታማኝ መጋቢ ስለነበረ ለጲጥፋራ ለመበልጸግ ምክንያት ሆኖ ነበር። ሌሎችን ለመርዳት የእግዚአብሔርን ሀብት የምንጠቀምባቸው መንገዶች አሉ።

የቅምጥል ኑሮ ይኖሩ ነበር (5፡5)፡- «በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል።» (የያዕቆብ 5፡5 ቀጥተኛ ትርጉም) መቀማጠል ማባከን ነው፤ ብኩንነት ደግሞ ኃጢአት ነው የሚል ነው።

አንድ ጋዜጣ ስለ አንድ በነዳጅ ሀብት የከበረ ሱልጣን የቅምጥል ኑሮ አውጥቶ ነበር። ካዲላክ የሚባሉ 19 መኪናዎችን ለ19 ሚስቶቹ ገዝቶ መኪናዎቹ ሽንጣም ሆነው እንዲሠሩለት ተጨማሪ ክፍያዎችን ከፍሎ ነበር። በተጨማሪ ሁለት ፓርስኪሶችን፥ ስድስት ማርቸዲሶችንና በ40 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ፈጣን ጀልባና ትልቅ ጎታች መኪና ገዝቶ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ 16 ማቀዝቀዣዎችን፥ 47ሺህ የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ የሴቶች ቁሳቁስ፥ ሁለት የፍሎሪዳ ብርቱካን ዛፎች፥ ሁለት ለመኝታም ሊሆኑ የሚችሉ ወንበሮችና ጣፋጭ ነገሮችን የሚያዘጋጅ መሣሪያ ገዛ። አጠቃላይ ወጪው 1 ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ነበር። ሁሉንም ነገሮች ወደ ስፍራው ለማጓጓዝ ደግሞ 194 ሺህ የአሜሪካን ዶላር መክፈል ነበረበት። ይህ እንዴት አስገራሚ የቅምጥል ኑሮ ምልክት ነው!

ሕይወት ለሚሰጡን መልካም ነገሮች ሁላችንም አመስጋኞች ነን። ወደ ቀድሞ ኑሮ ለመመለስ ማናችንም ብንሆን እንደማንፈልግ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ አንድ ነገር መጠኑ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ውጤቱ የሚመነምንበት ደረጃ መኖሩንም እንገነዘባለን። ኩዌከር የሚባለው የእምነት ቡድን አባል የሆነ አንድ ሰው ለጎረቤቱ እንዲህ አለው፡- «ለሕይወት አስፈላጊ ናቸው የምትላቸው ነገሮችን ንገረኝ እኔ ደግሞ ያለ

እነርሱ እንዴት መኖር እንደሚቻል እነግርሃለሁ።» ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- «የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከምንም ጆትም ሁሉ ተጠበቁ» (ሉቃስ 12፡15)። ያዕቆብ የሚናገርላቸው እነዚህ ሀብታሞች ድሆችን እስከ ሞት ድረስ እያስራቡ በእነርሱ ድካም ሀብትን ያከማቹ ነበር። በዚህ ቦታ ያለው የግሪኩ ቃል ለእርድ የሚቀለቡ ከብቶችን የሚያሳይ ነው።

እግዚአብሔር በሰጠን ነገር ሐሜት በማድረግ በመጠቀምና (1ኛ ጢሞ. 6፡17) ለሌሎች በመንፈግ በብኩንነት መኖር በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በእጃችን ያለው ሀብትና ንብረት በእግዚአብሔር ፈቃድ ያገኘነው ቢሆንም እንኳ በስስታምነት ልናባክነው አይገባም። ምክንያቱም በዙሪያችን የተቸገሩትን መርዳት አለብን።

ቅንጦት ሕይወትን የማበላሸት ባሕርይ አለው። እንደልብ የመኖር ውጤት ነው። ሀብትን በመልካም ባሕርይ ከያዝነው በርካታ መልካም ነገሮችን ማድረግ እንችላለን። ሀብትን ግን እንደፈለግን በመኖር ከያዝነው ውጤቱ ኃጢአት ነው። በሉቃስ 16፡19-31 ኢየሱስ የተናገረለት ሀብታም ሰው ያዕቆብ በዚህ ስፍራ ከሚገልጣቸው ሀብታሞች ጋር አንድ ዓይነት ናቸው።

ሀብታቸው የሚያስከትልባቸው ነገሮች (5፡1-4)

ሀብታሞች ማድረግ የቻሉትን ሁሉ ያደረጉት በሀብታቸው እንደሆነ ይመስላቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን «ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ» ይላቸዋል (5፡1)። ያዕቆብ ሀብትን ያለ አግባብ መጠቀም ስለሚያስከትላቸው ነገሮች ይናገራል።

ሀብት ሁሉ ይጠፋል (5፡2-3)፡- «ሀብታችሁ ተበላሽቶአል» (ቁጥር 2)። «ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል። ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል።» በዚህ ዓለም ያለ ማንኛውም ቁሳዊ ነገር ለዘለዓለም አይቆይም። የሞትና የመበስበስ ዘር በፍጥረት ሁሉ ውስጥ አለ።

በሀብት ዋስትና አለ ብሎ ማሰብ ትልቅ ስሕተት ነው። ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር፡- «በአሁኑ ዘመን ባለጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው» (1ኛ ጢሞ. 6፡17)። ሀብት ዋስትና የሌለው ነገር ነው። የገበያ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለዋወጣል። ስለዚህ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ ንብረቶችም ዋጋ እንዲሁ ይለዋወጣል። ወርቅ በእርግጥ እንደ

ብረት የሚዝግ ነገር አይደለም። አሳቡ ግን ያው ነው። ወርቅም ዋጋውን ይቀንሳል። በተጨማሪ ሕይወት አጭር ናት፤ ሀብትን ደግሞ ይዘን አንሄድም፤ ስለዚህ ለዚህ ዓለም ነገር መኖር ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ ለማየት እንችላለን። እግዚአብሔር ለሀብታሙ ሰው እንዲህ አለው፡- «አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል» (ሉቃስ 12፡20)።

ሀብትን ያለ አግባብ መጠቀም ባሕርይ ያጠፋል (5፡3)፡- «ዝገቱ ... ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል» (5፡3)። ይህ በጊዜው የተፈጸመ ፍርድ ነው። የሀብት መርዝ ስለ በከላቸው ወይም ስለ መረዛቸው በሕይወት እያሉ ተበልተዋል። ገንዘብ በራሱ ኃጢአት አይደለም። ለክፉትም ሆነ ለበጎነት የሚያገለግል ገለልተኛ ነገር ነው። «ገንዘብን መውደድ የክፉት ሁሉ ሥር ነውና» (1ኛ ጢሞ. 6፡10)። «አትመኝ» የሚለው ትእዛዝ ከአሥርቱ ትእዛዛት የመጨረሻው ቢሆንም ከሁሉም አደገኛ ነው። ምኞት አንድን ሰው የቀሩትን ዘጠኙንም ትእዛዛት እንዲጥስ የሚያደርግ ነው።

አብርሃም እምነቱንና ባሕርዩን የጠበቀ ሀብታም ነበር። ሎጥ ግን ሀብታም በሆነ ጊዜ ባሕርይው ተበላሸ፤ በመጨረሻም ቤተሰቡ ጠፋ። ሀብት ወደ ልብ ዘልቆ እስካልገባ ድረስ በእጅህ መኖሩ መልካም ነው። «ባለጠግነት ቢበዛ ልባችሁ አይኩራ» (መዝ. 62፡10)። «መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይሻላል፥ መልካምም ሞገስ ከብርና ከወርቅ ይበልጣል» (ምሳሌ 22፡1)።

ፍርድ የማይቀር ነው (5፡3-5)፡- ያዕቆብ የተመለከተው በጊዜው የተሰጠውን ፍርድ ብቻ አልነበረም። በጊዜው የተሰጠው ፍርድ የሀብታቸው መበስበስና የባሕርያቸው መበላሸት ነበር። በእግዚአብሔር ፊት ወደፊትም የሚመጣ ሌላ ፍርድ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈራጅ ይሆናል (5፡9) ፍርዱም በጽድቅ ይሆናል።

በዚያ የፍርድ ቀን እግዚአብሔር የሚጠራቸውን ምስክሮች ልብ በል። በመጀመሪያ ደረጃ የሀብታሞቹ ሀብት በእነርሱ ላይ ይመሰክርባቸዋል (5፡3)። የተበላሸው ሀብታቸው፥ የዛገው ብርና ወርቃቸው፥ በብል የተበላው ልብሳቸው እጅግ ስስታም በሆነው ልባቸው ላይ ይመሰክርባቸዋል። እዚህ ላይ ሀብታሞች ይረዷቸው ዘንድ ሀብታቸውን ቆጥበው አከማቹ፤ ይህ በስግብግብነት የተከማቸው ሀብት ግን በእነርሱ ላይ ይመሰክርባቸዋል የሚለውን የምጸት አነጋገር ያስታውሰናል።

ከሠራተኞች ያስቀሩት ገንዘብ ይመሰክርባቸዋል (5:4)። ገንዘብ ይናገራል እነዚህ የተሰረቁ ደመወዞች ለጽድቅና ለፍርድ ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ። እግዚአብሔር የአቤል ደም ከምድር ሲጮህ ሰማ (ዘፍ. 4:10)፤ ይህ የተሰረቀ ገንዘብ በሚጮህበት ጊዜም ይሰማል።

ሠራተኞችም በእነርሱ ላይ ይመሰክራሉ (5:4)፡- እነዚህ ሀብታሞች ምስክሮቹንም ሆነ እውነተኛው ፈራጅ እግዚአብሔርን ጉቦ በመስጠት ከጎናቸው ሊያቆሙ የሚችሉበት መንገድ የለም። እግዚአብሔር የጭቁኖችን የጩኸት ድምፅ ይሰማል። በጽድቅም ይፈርዳል።

ይህ ፍርድ ከባድ ነገር መሆኑ እውን ነው። በኃጢአታቸው የጠፉ ሰዎችም በክርስቶስ የነጭ ዙፋን ፍርድ ፊት ይቆማሉ (ራእይ 20:11-15)። የዳኑት በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቆማሉ (ሮሜ 14:10-12፤ 2ኛ ቆሮ. 5:9-10)። እግዚአብሔር በኃጢአታችን ላይ አይፈርድም፤ ምክንያቱም ኃጢአታችን ቀደም ብሎ በክርስቶስ መስቀል ላይ ተፈርዶበታል። እንደ ክርስቲያን የሚፈረድብን በሥራዎቻችንና በአገልግሎታችን ነው። እርሱን በማገልገልና በማክበር ታማኞች ከሆንን ሽልማትን እናገኛለን። ታማኝ ካልሆንን ግን ደኅንነታችንን ባናጣም እንኳ ሽልማታችንን እናጣለን (1ኛ ቆሮ. 3:1-15)።

የመልካም ዕድል መታጣት (5:3)፡- «ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል» የሚለው ቃል ያዕቆብ የጌታ መምጣት ቅርብ መሆኑን ያምን እንደነበር ያሳየናል (5:8-9 ተመልከት)። የኤፌ. 5:16 ቀጥተኛ ትርጉም እንደሚያመለክተን «መልካም ዕድሎችን መዋጀት» አለብን። ደግሞም ቀን እያለ መሥራት አለብን ማለት ነው (ዮሐ. 9:4)። ያለ አግባብ በተከማቸው ሀብት ምን ሊሠራ ይችል እንደነበረ አስብ። ሊረዱ የሚገባቸው ድሆች በዚያ ጉባኤ ውስጥ ነበሩ (ያዕ. 2:1-6)። የድካማቸውን ዋጋ ሊያገኙ የሚገባቸው ሠራተኞች ነበሩ። ብዙም ሳይቆይ የአይሁድ ሕዝብ መሸነፋቸውና መበተናቸውን ኢየሩሳሌምም መጥፋቷን መመልከት የሚያሳዝን ነገር ነው።

በገንዘብ ልትገዛቸው የማይቻሉ ነገሮች ሊኖሩህ እንደሚገባ ሁሉ በገንዘብ ልትገዛቸው የሚቻሉ ነገሮች ደግሞ እንዲኖሩህ ያስፈልጋል። 500 መቶ ሺህ ብር የሚያወጣ ሕንፃ መገንባት ቢቻልና ቤተሰብ ከሌለ ምን ይጠቅማል? ፍቅር ሳይኖር አንድ ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የአልማዝ ቀለበት ማድረግ ምን ይጠቅማል? ያዕቆብ ሀብታሞችንና ሀብትን አላወገዘም። ነገር ግን ያወገዘው ሀብትን በተሳሳተ መንገድ መጠቀምና

ሀብታቸው ለመልካም ነገር መገንቢያ መሣሪያ ሳይሆን ሌላውን ለመጉጂያ የሚጠቀሙበትን ነው።

በዚህ ዓለም ደሀ መሆንና በሚቀጥለው ዓለም ግን ሀብታም መሆን ይቻላል (2፡5)። በዚህ ዓለም ሀብታም ሆኖ (1ኛ ጢሞ. 6፡17) በሚቀጥለው ዓለም ደሀ መሆንም ይቻላል። የጌታ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ሰዎችን በልባቸው እንዳለው መንፈሳዊ ሁኔታ፥ አንዳንዶችን ሀብታም ሌሎችን ደግሞ ድሀ ያደርጋል። «መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናል» (ማቴ. 6፡21)።

የምናጠራቅመው ይጠፋብናል፥ ለእግዚአብሔር የምንሰጠውን ደግሞ እርሱ ይጠብቅልናል። በእዚያም ላይ ወለድን ይጨምርበታል። ረጃጅም ስብከቶችን በመስበክ የታወቀ አንድ ሰባኪ ዓመታዊውን «ቸርነትን የማድረግ ስብከት» ለድሆች እንዲሰብክ ተጠየቀ። መልእክቱን ካራዘመ ጉባኤው መስጠት ያለበትን ያህል ላይሰጥ እንደሚችል ተነገረው።

የዕለቱ ሰባኪ የመልእክቱ ክፍል የሆነውን ምሳሌ 19፡17 እንዲህ ሲል አነበበ፡- «ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፥ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል።» መልእክቱንም በጣም አጭርና ግልጽ በሆነ መልኩ፡- «በአሳቡ ደስ የተሰኛችሁ ከሆነ ስጡ» በማለት ዘጋ።

አዎን ገንዘብ ይናገራል። በመጨረሻው የፍርድ ቀን ይህ የሚናገር ገንዘብ እናንተንስ ምን ይላችሁ ይሆን?

ያዕቆብ 5:7-12

«እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ። እነሆ፥ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል። እናንተ ደግሞ ታገሡ፥ ልባችሁንም አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና። ወንድሞች ሆይ፥ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፤ እነሆ፥ ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል። ወንድሞች ሆይ፥ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ። እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።

«ከሁሉም በፊት፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ በሰማይ ቢሆን በምድርም ቢሆን በሌላ መሐላም ቢሆን በምንም አትማሉ፤ ነገር ግን ከፍርድ በታች እንዳትወድቁ ነገራችሁ አዎን ቢሆን አዎን ይሁን፥ አይደለምም ቢሆን አይደለም ይሁን።»

-12-

የትዕግሥት ኃይል

ያዕቆብ መከራ እየተቀበሉ ላሉት ቅዱሳን «ታገሡ» በማለት ይጽፍላቸዋል። ይህ በመልእክቱ መጀመሪያ ላይ የሰጣቸው ምክር ነበር (1፡1-5)። ደግሞም መልእክቱን ለማጠቃለል ሲቃረብ ይህንኑ ምክር ይመክራቸዋል። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ በዚህ ዓለም ላይ ያሉት ስሕተቶች በሙሉ አያስተካክልም፤ ስለዚህ አማኞች ይህ ጊዜ እስኪደርስ በትዕግሥት ልንጸናና በተስፋ ልንጠባበቅ ይገባል።

ያዕቆብ ሦስት ጊዜ ያህል ስለ ጌታ መምጣት ያሳስበናል (5፡7፥ 8 ና 9)። ይህም ለእኛ ለአማኞች «የተባረከ ተስፋችን» ነው (ቲቶ 2፡13)። በምድራዊ ሕይወታችን ሁሉ ነገር ቀላልና ምቹ እንዲሆን አንጠብቅም፤ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» ተብሎ ተነግሮናል (ዮሐ 16፡33)። ጳውሎስ ወደ ጌታ ያመጣቸውን ሰዎች «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» (የሐዋ. 14፡22) በማለት ይመክራቸዋል። ኢየሱስ እስኪመለስ ድረስ አስቸጋሪና አስጨናቂ ነገሮችን በትዕግሥት ልንቀበል ያስፈልጋል።

ያዕቆብ ትዕግሥትን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ሁለት የተለያዩ ቃላት ናቸው። በቁጥር 7፥ 8 እና 10 ለማዘን ወይም ለመቆጣት የመዘግየት አሳብ ሲሆን በቁጥር 11 ላይ ያለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉም «በአንድ ነገር ውስጥ መቆየትን» የሚያመለክት ይሆናልና በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ያሉበትን ሁኔታ መቻል ወይም መቋቋም እንደሆነ ያሳስባል። ትዕግሥት ማለት «ለመሸሽ እየፈለጉ ወይም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች እያሉ ጸንቶ መቆየትን ወይም መቋቋም» ነው። በርካታ የግሪክ ቋንቋ አዋቂዎች በቁጥር 7፥ 8 እና 10 ላይ ያለው፥ ሰዎችን መታገሥን የሚያመለክት ሲሆን በቁጥር 11 ላይ ያለው ግን ሁኔታዎችን ወይም ነገሮችን መታገሥን የሚያመለክት ነው ይላሉ።

ልንመልሰው የሚገባን ጥያቄ ግን እንደ ክርስቲያን የጌታን መምጣት ስንጠባበቅ ይህንን ትዕግሥት ልንለማመደው የምንችለው እንዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ ነው። ያዕቆብ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ በትዕግሥት እንድንጸና ለማበረታታት ሦስት ምሳሌዎች ይሰጠናል።

ገበሬ (5፡7-9)

አንድ ሰው ታጋሽ ካልሆነ ገበሬ ባይሆን ይሻለዋል። ምናልባት ዐረም ካልሆነ በስተቀር በአንድ ሌሊት የሚበቅል ነገር የለም። የዕለቱ የአየር ሁኔታ ለመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ገበሬም አይገኝም። ብዙ ዝናብ ምርትን ሊያደርቀው ይችላል። ብዙ ፀሐይ ደግሞ ምርቱን ሊያደርቀው ይችላል። ወይም ደግሞ ገና ሳይደርስ ውርጭ ሰብሉን ሊያጠፋ ይችላል። አንድ ገበሬ የአየር ሁኔታውን ምን ያህል ሊታገሥ ይገባው ይሆን!

አንድ ተክል እንዲበቅል ጊዜ ይወስዳልና ዘሩንና ሰብሉንም መታገሥ ያስፈልገዋል። አይሁዳውያን ገበሬዎች መሬታቸውን የሚያዘጋጁትና ዘር የሚዘሩት በበልግ ወራት ነበር። «የበልግ ዝናብ» በመባል የሚታወቀው ዝናብ መሬቱን ሊያለሰልሰው ይገባል። የመኸር ዝናብ ደግሞ በጸደይ ወራት ይመጣና ሰብሉ እንዲበስል ይረዳዋል። አንድ ገበሬ የዘራው ዘር ፍሬ እስኪሰጥ ድረስ በርካታ ወራቶችን መታገሥ አለበት።

ገበሬው በፈቃደኝነት ለረጅም ጊዜ መጠበቅ ያለበት ለምንድን ነው? ምክንያቱም ፍሬው የከበረ ነው (5፡7)። የሰብል ምርት በትዕግሥት ሊጠበቅ የሚገባው ነው። «ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና» (ገላ. 6፡9)። «ምድሪቱም አውታ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ፥ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች። ፍሬ ግን ሲበስል መከር ደርሶአልና ወዲያው ማጭድ ይልካል» (ማር. 4፡28-29)።

ያዕቆብ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ሰብልን የሚጠብቅ «መንፈሳዊ ገበሬ» አድርጎ አቅርቦታል። «እናንተ ደግሞ ታገሡ፥ ልባችሁን አጽኑ ...» (ያዕ. 5፡8)። መሬቱ ልባችን ሲሆን ዘሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ሉቃስ 8፡11)። ለመሬት የተለያዩ ወቅቶች እንዳሉ ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወትም የተለያዩ ወቅቶች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ልባችን እንደ ክረምት መሬት ይሆናል። ስለዚህ እግዚአብሔር ዘሩን ከመዝራቱ በፊት ልባችንን ሊያዘጋጅ ያስፈልጋል (ኤር. 4፡3)። የተዘራውን ዘር እንዲበቅል ደግሞ የቸርነቱን ፀሐይና ዝናብ በመላክ ይመግበዋል፥ ያረሰርሰዋልም። ሰብሉን ለመሰብሰብ ግን አሁንም መታገሥ አለብን።

መንገዱ አስቸጋሪና ከባድ በሚሆንበት ጊዜ የትዕግሥት ምሥጢሩ እግዚአብሔር በሕይወታችን ሰብሉን እያዘጋጀ እንደሆነ መገንዘብ ነው።

እግዚአብሔር በሕይወታችን የመንፈስ ፍሬ እንድናፈራ ይፈልጋል (ገላ. 5፡22-23)። ይህንን የሚያደርግ ብቸኛ መንገድ መከራና ችግር ነው። በእግዚአብሔርና በራሳችን ላይ ትዕግሥት የለሾች ከመሆን ይልቅ እራሳችንን ለጌታ ልናስረክብና ፍሬው እንዲያድግ ልንፈቅድ ያስፈልጋል። ሰብሉን የምንጠብቅ «መንፈሳዊ ገበሬዎች» ነን።

እንዲህ ዓይነቱን ሰብል በማምረት ደስ ልትሰኝ የምትችለው ልብህን ስታጸና ብቻ ነው (ያዕ. 5፡8)። ከአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ዓላማዎች መካከል አንዱ ልብን ማጽናት ነው (ሮሜ. 1፡11)። ጳውሎስ በተሰሎንቄ የሚገኙትን አዳዲስ አማኞች በእምነታቸው ለማጽናት (1ኛ ተሰ. 3፡1-3) ጢሞቴዎስን ላከላቸው። ደግሞም እንዲጸኑ ጸለየላቸው (1ኛ ተሰ. 3፡10-13)። ልብን ለማጽናት የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት አስፈላጊ ናቸው። ያልተረጋጋ ልብ ፍሬን ማፍራት አይችልም።

አንድ ገበሬ ምርቱን እስኪያገኝ ድረስ ሥራ ፈትቶ ዝም ብሎ እንደማይቀመጥ አስታውስ። የሰብሉን ምርት ለማፈስ እየተጠባበቀ ያለማቋረጥ በሥራ ይጠመዳል። ያዕቆብ እነዚህ በመከራ ውስጥ የነበሩ ክርስቲያኖች ነጭ ልብሳቸውን ለብሰው ተራራ ላይ በመውጣት የጌታን መምጣት እንዲጠባበቁ አላስተማራቸውም «እየሠራችሁ ተጠባበቁ» በማለት መከራቸው እንጂ። «ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው» (ሉቃስ 12፡43)።

ገበሬ ከጎረቤቶቹ ጋር ጠብአይፈጥርም።ገበሬዎችየሚታወቁበትአንድ የተለመደ መለያቸው እርስ በእርስ ለመረዳዳት ያላቸው ፈቃደኛነትነው። እርስ በእርስ ለመጣላትና ለመከራከር ጊዜም ሆነ ጉልበት የላቸውም። ያዕቆብ በምዕ. 5፡9 ላይ «እንዳይፈረድባችሁ እርስ በእርሳችሁ አታጉረምርሙ» ሲል ይህን አሳብ በአእምሮው ይዞ ሳይሆን አይቀርም። እግዚአብሔርን በትዕግሥት የማንጠብቅ ከሆነ ከሰዎችም ጋር ባለን ግንኙነት ትዕግሥት አይኖረንም። ይህ ልናስወግደው የሚገባ ኃጢአት ነው። እርስ በእርሳችን መጣላት ከጀመርን ምርታችንን እናጣለን።

ነቢያት (5፡10)

ያዕቆብ መልእክቱን የጻፈላቸው የአይሁድ ጉባኤ በዚህ ስፍራ የሚጠቅሰውን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ጉዳይ በቀላሉ ሊገነዘቡት ይችላሉ። ኢየሱስም በተራራው ስብከት ላይ ነቢያትን በስደት ላይ ድል

የመንግት ምሳሌ አድርጎ አቅርቦአቸዋል (ማቴ. 5፡10-12)። ከምሳሌነታቸው ምን ማጽናኛ እናገኝ ይሆን?

በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ቢሆኑም እንኳ መከራን ተቀበሉ። «በጌታ ስም» እየሰበኩ መከራን ይቀበሉ ነበር። ሰይጣን ታማኝ የሆኑ ክርስቲያኖችን መከራ የሚቀበሉት በኃጢአታቸው ወይም ታማኝ ባለመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ አድርጎ ያሳያቸዋል። ሆኖም ግን መከራን የሚቀበሉት በታማኝነታቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል። «በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ» (2ኛ ጢሞ. 3፡12)። መታዘዝ ወዲያውኑ ነገሮችን የሚያቃልልልንና መዝናናትን የሚፈጥርልን እንደሆነ ማሰብ የለብንም። ጌታችን ኢየሱስ ታዛዥ ነበር። ታዛዥነቱ ግን ወደ መስቀል መራው።

ነቢያት የሚያስታውሱን ለእግዚአብሔር ብለን መከራን በምንቀበልበት ጊዜ እርሱ እንደሚጠነቀቅልን ነው። ኤልያስ ክፉ ለነበረው ንጉሥ ለአክአብ በምድሪቱ ለሦስት ዓመት ተኩል ድርቅ እንደሚኖር አስታወቀው፤ ኤልያስ እራሱም በዚህ ድርቅ ዘመን መከራን መቀበል ነበረበት። ነገር ግን እግዚአብሔር ተጠነቀቀለት፤ በክፉዎቹ የበአል ነቢያትም ላይ ድልን ሰጠው። እንዲህ የሚል አባባል አለ፡- «የእግዚአብሔር ፈቃድ የእግዚአብሔር ጸጋ ሊጠብቅህ ወደማይችልበት ስፍራ ሊመራህ ከቶ አይችልም።»

አብዛኛዎቹ ነቢያት ከፍተኛ መከራና ችግርን ተቀብለዋል። በማያምኑ ብቻ ሳይሆን አማኝ ነን ብለው በሚናገሩ እጅ እንኳ መከራ ደርሶባቸዋል። ኤርምያስ እንደ ሰላይና ጠላት ተቆጥሮ ተያዘና እንዲሞት ሰው በማይደርስበት ጉድጓድ ተጥሎ ነበር። እግዚአብሔር ኤርምያስን መገበው። ኢየሩሳሌም በጠላቶችዋ በተከበበችበት በዚያ አስጨናቂ ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ኤርምያስን ጠብቆታል። ሕዝቅኤልና ዳንኤልም የራሳቸውን የመከራ ድርሻ ተቀብለዋል። እግዚአብሔር ግን ታድጎአቸዋል። እግዚአብሔር ያልታደጋቸው ማለትም ለእምነታቸው የሞቱትም እንኳ ለእርሱ እውነተኛ ሆነው የሚቆዩት ሁሉ የሚቀበሉትን ሽልማት ተቀብለዋል።

በጌታ ስም የሚናገሩ ሁሉ ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ መከራና ፈተና የሚገጥማቸው ለምንድን ነው? ሕይወታቸው መልእክታቸውን ለመደገፍ እንዲችል ነው። ታማኝ የሆነና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው

ሕይወት ከፍተኛ ኃይል አለው። በመከራ ጊዜ መታገሣችን በዙሪያችን ለሚኖሩ ሰዎች ምስክር እንደሚሆን ልናስታውስ ያስፈልጋል።

ግንም የሚያስብላቸው ሳይኖር ብዙ ታማኝ ክርስቲያኖች የተለያየ መከራ ተቀብለው የለም? አዎን ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ግን እነዚህ የተሰወሩ ጀግኖች ሽልማታቸውን ይቀበላሉ። ነቢያት ተገድለዋል ተቀብረዋል ዛሬ ግን ስማቸው ይከበራል። ጌታችን በሚመለስበት ጊዜ ያዘጋጀውን ሽልማት ይዞ ይመጣል (ራእይ 22፡12)።

ያዕቆብ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የሚጠቅሳቸው ምሳሌዎች መጽሐፍ ቅዱስን በይበልጥ እንድናጠናና እነዚህን የእምነት አርበኞች ይበልጥ እንድናውቃቸው ያበረታታናል። «ለመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» (ሮሜ 15፡4)። መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ባወቅን ቁጥር በሕይወት አስቸጋሪ ልምምዶች ውስጥ ብናልፍም እግዚአብሔር የበለጠ ያበረታታናል። ዋናውና እጅግ አስፈላጊው ነገር ሁኔታዎቹ ምንም ያህል ፈታኝ ይሁኑ እንደ ገበሬው መትጋትና እንደ ነቢያት በምስክርነታችን መጽናት ነው።

ኢዮብ (5፡11)

«እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን» (5፡11)። በሕይወትህ ፈተና ከሌለ ደግሞ መጽናት አትችልም። ያለ ጦርነት ድል ሊኖር አይችልም፤ ያለ ሽለቆ የተራራ ጫፍ ሊኖር አይችልም። በረከትን ወይም ብፁዕ መባልን ከፈለግህ ሽክምን ለመሸከምና ጦርነቱን ለመዋጋት የተዘጋጀህ መሆን አለብህ።

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ክርስቲያን እንዲህ ብሎ ሲጸልይ ሰማሁት፡- «ጌታ ሆይ እባክህን የቃልህን ጥልቅ ትርጉም አስተምረኝ። ወደ ሰማያት ወጥቼ በዚያ የሚገኙትን አስደናቂ ነገሮች ለመስማትና ለማየት እፈልጋለሁ»። ይህ ጸሎት ከእውነተኛ ልብ የሚወጣ ንጹሕ ጸሎት ነው። ሆኖም ይህ ወጣት ሰው ምን ይጸልይ እንደነበር አላስተዋለም። ጳውሎስ ወደ ሦስተኛው ሰማይ ተነጠቀና በቃላት ሊገለጹ እጅግ የሚያስቸግሩ አስደናቂ ነገሮችን ተማረ፤ በውጤቱም እንዳይታበይ ለሥጋው መውጊያ ተሰጠው (2ኛ ቆሮ. 12፡1-10)። እግዚአብሔር ኃላፊነትንና መብትን፥ በረከትንና የአገልግሎት ሽክምን አብሮ ነው የሚሰጠን። አለበለዚያ እኔና አንተ ብልሹና ቀበጥ ነው የምንሆነው።

«በረከቶች» የሚመጡት መቼ ነው? በፈተናችንና መከራ በምንቀበልባቸው ጊዜያት የእግዚአብሔርን በረከቶች ልንለማመድ እንችላለን። በእቶን እሳት ውስጥ የተጣሉት ሦስቱ ወጣት ዕብራውያን የተለማመዱትም ይህ ነበር (ዳን. 3)። እንደ ያዕቆብ አመለካከት ደግሞ በረከት የሚመጣው በምሳሌነት እንደተጠቀሰልን እንደ ኢዮብ በፈተና ከጸናን በኋላ ነው።

መጽሐፈ ኢዮብ ረጅም መጽሐፍ ነው። ምዕራፎቹ ለምዕራባውያን አእምሮ አድካሚና አሰልቺ በሚመስሉ ረጃጅም ንግግሮች ተሞልተዋል። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች የኢዮብን ኃዘን እንመለከታለን። ሀብቱን፥ መላ ቤተሰቡንና ጤንነቱን አጥቶ ነበር። የቀረበችው ራሱን እንዲገድል የመከረችው ሚስቱ ብቻ ነበረች። ከምዕራፍ 4-31 ከሦስቱ ጓደኞቹ ጋር በሚከራከርበት ጊዜ ለሐሰተኛ ክሳቸው የሰጠውን መከላከያ እናገኛለን። ከምዕራፍ 38-42 የኢዮብን መዋጀት እንመለከታለን። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ኢዮብን ትሑት አደረገው፤ ከዚያ በኋላ ግን ኢዮብን አከበረውና ከዚህ ቀደም ከነበረው ሁለት ዕጥፍ ሰጠው።

የኢዮብን ሥቃይ በምናጠናበት ጊዜ ኢዮብ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ስለተፈጸመው ውይይት የሚያውቀው አንዳችም ነገር እንደሌለ ማስታወስ ጠቃሚ ነው። የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብን ኃጢአተኛና ግብዝ አድርገው ከሰሱት። «በሕይወትህ እጅግ ክፉ የሆነ ኃጢአት ባትፈጽም ኖሮ እግዚአብሔር ይህ ሁሉ መከራ እንዲደርስብህ አይፈቅድም ነበር» በማለት ተከራከሩት። በክርክራቸው ሁሉ ኢዮብ እስከመጨረሻው ድረስ፤ ጥፋተኛ እንዳልሆነ ገለጸ። ፍጹም ነኝ ግን አላለም። ጓደኞቹ ሁሉ ተሳስተው ነበር። እግዚአብሔር ለዚህ ሁሉ ችግር ምክንያት የሚሆን በኢዮብ ላይ ያየው ጥፋት አልነበረም (ኢዮብ 2፡3)። በመጨረሻ ስለ ኢዮብ በተናገሩት ሐሰተኛ ነገር እግዚአብሔር ጓደኞቹን ገሠጻቸው (ኢዮብ 42፡7)።

ከኢዮብ የላቀ ታላቅ መከራን የተቀበለ ምሳሌ ለማግኘት አስቸጋሪ ነው። ሀብቱንና ጤንነቱን በሙሉ ስላጣ ሁኔታዎች ሁሉ በእርሱ ላይ ተነሥተውበት እንደነበር ግልጽ ነው። ተወዳጅ ልጆቹን በሙሉ አጥቶ ነበር። ሚስቱም እንኳ «እግዚአብሔርን ስደብና ሙት» (ኢዮብ 2፡9) አለችው እንጂ ድጋፍን አልሰጠችውም ነበር። ጓደኞቹም የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገባው ግብዝ ሰው ነው በማለት በርሱ ላይ ተነሥተው ነበር። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔርም እንኳ በእርሱ ላይ እንደተነሣ ይመስል

ነበር። ኢዮብ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመፈለግ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኽ ለጊዜው ከሰማይ የመጣ መልስ አልነበረም።

ሆኖም ኢዮብ በፈተናው ጸና። ሰይጣን ግን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት እንዲጥል አቀደ፤ ነገር ግን አልተሳካለትም። ኢዮብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእርግጥ ጠይቋል፤ እምነቱን ግን ጨርሶ አልጣለም፡- «እነሆ ቢገድለኝም እንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠብቃለሁ ነገር ግን መንገዴን በፊቱ አጸናለሁ» አለ (ኢዮብ 13፡15)። ኢዮብ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር በሙሉ ባይረዳም እንኳ እግዚአብሔር ፍጹም እንደሆነ በጣም እርግጠኛ ነበር። ከእርሱ ጋር መከራከሩን ግን ቀጥሎ ነበር። መጽናት ማለት ይህ ነው።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነበር። ሕግጋቱን ከጠበቁ እንደሚባርካቸው በቃል ኪዳኑ ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር (ዘዳ. 11)። ይህ አሳብ ሀብትና ምቹ ኑሮ ካለህ በእግዚአብሔር ተባርከሃል ማለት ነው፤ ደሀና በመከራ ውስጥ ከሆንህ ደግሞ በእግዚአብሔር ተረግመሃል ማለት ነው ወደሚል ነገር ይመራናል። የሚያሳዝነው ነገር ዛሬም ቢሆን ብዙ ሰዎች የዚህ የተሳሳተ አሳብ አራማጆች ናቸው። ሀብታም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባ ዘንድ በጣም አስቸጋሪ ነው ብሎ ኢየሱስ ሲናገር ደቀ መዛሙርቱ ደነገጡ። «ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?» (ማቴ. 19፡23-28) በማለትም ተጠያየቁ። በዚያን ጊዜ በተለይ ሀብታሞች በእግዚአብሔር የተባረኩ ናቸው የሚል የተሳሳተ አሳብ ነበር። ስለዚህ እነርሱ ሊገቡ ካልቻሉ ማንም ሊገባ አይችልም አሉ።

መጽሐፈ ኢዮብ ያንን አሳብ ይቃወማል። ኢዮብ ጻድቅ ሰው ቢሆንም መከራን ግን ተቀበለ። እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ አንዳችም ክፉ ነገር አላገኘም፤ ሰይጣንም እንኳ አንዳች ሊያገኝበት አልቻለም። የኢዮብ ወዳጆችም ክሳቸውን የሚያረጋግጡበት ነጥብ አልነበራቸውም። የኢዮብ መጽሐፍ እግዚአብሔር ኃጢአትን ከመቅጣት ይልቅ በመከራ ውስጥ ታላላቅ ዓላማዎች እንዳሉት ያስተምረናል። በኢዮብ ላይ የደረሰው መከራ ለኃጢአቱ ሳይሆን ለዚህ ዓለም ኃጢአት መከራ የተቀበለውን የፍጹሙን የእግዚአብሔርን ልጅ መንገድ ጉልህ ለማድረግ ነው።

በኢዮብ ሕይወት የጌታ የመጨረሻ ዓላማ ምን ነበር? እግዚአብሔር ፍጹም ርኅሩኅና መሐሪ እንደሆነ መግለጥ ነበር። ከኢዮብ ሥቃይ የምናያቸው ሌሎች ውጤቶችም መኖራቸው እርግጥ ነው፤

እግዚአብሔር የቅዱሳኑን መከራና ችግር እንዲሁ አያልፍም። ኢዮብ እግዚአብሔርን በአዲስና በጥልቅ መንገድ ተገናኘው (ኢዮብ 42፡1-6)። ከዚያም በኋላ ኢዮብ ታላላቅ በረከቶችን ከጌታ ተቀበለ።

እግዚአብሔር ምሕረትን የተሞላ ከሆነ ኢዮብን ከዚያ ሁሉ መከራ ለምን አልጠበቀውም? የሚል ክርክር ሊነሣ ይችላል። በእርግጥ በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ይህ ውስን አእምሮአችን ሊረዳቸው የማይችላቸው ምሥጢራት አሉ። ነገር ግን አንድ ነገርን እናውቃለን፡- ኢዮብ በዚሁ ከባድ ሥቃይ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ይህ ሥቃይ እግዚአብሔር እንዲከበር ኢዮብ ደግሞ በሕይወቱ እንዲጠራ አድርጎታል። ልትታገሥና ልትጸናበት የምትችለው ነገር እስከሌለ ድረስ መጽናትና መታገሥን አትማርም።

ያዕቆብ መልእክቱን ለጻፈላቸው አማኞችና ዛሬ ደግሞ ለእኛ የኢዮብ ታሪክ ምን ያስገነዝበናል? በሕይወታችን ከሚያጋጥሙን መከራዎች አንዳንዶቹ በቀጥታ በሰይጣን ተቃውሞ የሚመጡ መሆናቸውን ያስገነዝበናል። እግዚአብሔር ልጆቹ በሰይጣን እንዲፈተኑ ይፈቅዳል፤ ነገር ግን ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች የሚፈትንበትን ሥልጣንና ኃይል ሁልጊዜ ገደብ ያበጅለታል (ኢዮብ 1፡12 ና 2፡6)። በማንኛውም ጊዜ እራስህን በመከራ ውስጥ ስታገኘው በጸጋ የተሞላ የእግዚአብሔር እጅ ሁኔታውን እንደሚቆጣጠር አትዘንጋ። «የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ» (ኢዮብ 23፡10)።

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ትዕግሥት የለሾች እንድንሆን ሊያደርገን ይፈልጋል፤ ትዕግሥት የሌለው ክርስቲያን ደግሞ በዲያብሎስ እጅ ያለ ኃይለኛ መሣሪያ ነው። ከምዕ. 1 ጥናታችን እንደምታስታውሰው የሙሴ ትዕግሥት ማጣት ወደ ተቀደሰችው ምድር እንዳይገባ አግዶታል፤ የአብርሃም ትዕግሥት ማጣት የአይሁድ ጠላቶች አባት የሆነው የእስማኤልን መወለድ አስከትሏል፤ የጴጥሮስ ትዕግሥት ማጣት ደግሞ በእጁ የሰው ሕይወት እንዲጠፋ ሊያደርገው ነበር። ሰይጣን በሚያጠቃን ጊዜ ትዕግሥት በማጣት የእግዚአብሔርን በረከት ሊያሳጣን የሚችለውን እርምጃ ከእግዚአብሔር ቀድመን እንድንወስድ ያደርገናል።

ታዲያ ለዚህ ጉዳይ መልሱ ምንድን ነው? «ጸጋዬ ይበቃሃል» (2ኛ ቆሮ. 12፡7-9)። የጳውሎስ የሥጋው መውጊያ «የሰይጣን መልእክተኛ» ነበር። ጳውሎስ መልሶ ሊዋጋው፥ እጁን ሊሰጥ፥ ወይም

መውጊያው እንደሌለ አድርጎ መካድ ይችል ነበር። ነገር ግን አላደረገውም። በዚህ ሁሉ ፈንታ በሚያስፈልገው በእግዚአብሔር ጸጋ ታመነ። የሰይጣንንም መውጊያ መንፈሳዊ ሕይወቱን መገንቢያ መሣሪያ አድርጎ ተጠቀመበት።

እራሳችሁን በከፍተኛ የእቶን እሳት ውስጥ ስታገኙ ወደ ጸጋው ዙፋን ፊት በመቅረብ ለመጽናት የሚያስፈልጋችሁን ጸጋ ከጌታ ተቀበሉ (ዕብ. 4፡14-16)። በምታልፍበት መከራ ሁሉ እግዚአብሔር ጸጋን የተሞላ ዓላማ እንዳለውና እነዚህን ዓላማዎቹን በጊዜው ለክብሩ እንደሚሠራቸው አስታውስ። በማታውቀው ጉዳይ የተጠመድክ በጨካኝ ጌታ ሥር እንዳለህ አድርገህ ራስህን አትገምት። የአስደናቂው የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል የመሆን መብትን ያገኘህ ተወዳጅ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። በሁለቱም መካከል ልዩነት አለው!

በቁጥር 12 «ስለ መሐላ» የተነገረው ቃል ከመከራ ጋር ምን ያያይዘዋል? የሚል ጥያቄ የሚያስነሣ ያለቦታው የገባ ነገር ይመስላል። ከዚህ ቀደም መከራን ተቀብለህ ከሆነ ግን መልሱን ታውቀዋለህ። በመከራና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ እግዚአብሔርን የማግባቢያና የማይፈጸም ተስፋ እንኳ ልትሰጥ ትችላለህ። ለምሳሌ ወደ ኢዮብ ተመልሰህ ስለ እርሱ አስብ። ይህ የእምነት አባት እንዲህ አለ፦ «ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፥ ራቁቴን ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን። በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፥ ለእግዚአብሔርም ስንፍናን አልሰጠም» (ኢዮብ 1፡21-22)። ኢዮብ የተወለደበትን ቀን ረግሞአል (ኢዮብ 3፡1-26)። እግዚአብሔርን ግን ጨርሶ አልሰደበም፤ ብልህነት የጎደለው መሐላም አላደረገም። እግዚአብሔርን ለማግባባት የማይረባ ነገር ለማድረግ አልሞከረም።

ያዕቆብ ይህን ያለው ኢየሱስ በተራራው ስብከት ያስተማረውን ነገር እያስታወሰን መሆኑ ግልጽ ነው (ማቴ. 5፡34-37)። አይሁዶች የተናገሩትን ነገር በመሐላ በማጽናት የታወቁ ናቸው። ሆኖም ግን በመሐላቸው የእግዚአብሔርን ስም ላለመጠቀም እጅግ ጠንቃቃ ነበሩ። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት እግዚአብሔርን መሳደብ ነውና። ስለዚህ በሰማይ ወይም በምድር ወይም በኢየሩሳሌምም በራሳቸው እንኳ ይምሉ ነበር። ኢየሱስ ግን በእንደዚህ ዓይነት መሐላዎች ውስጥ እግዚአብሔርን ማገልገል የማይቻል እንደሆነ አስተማረ። ሰማይ ዙፋኑ፤ ምድር መረገጫው ኢየሩሳሌምም «የታላቁ

ንጉሥ ከተማ» ናትና። በራስስ መማል ምን መልካምነት አለው? «አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ማድረግ አትችልምና» (ማቴ. 5፡36)፤ ወይም አንዲት ጠጉር በራስህ ላይ ለማብቀል አትችልምና።

የእውነተኛ ክርስቲያን ባሕርይ ጥቂት ብቻ መናገር ነው የሚለው መሠረታዊ መመሪያ ነው። አንድ ነገርን ለማሳመን በመሐላ በርካታ ቃሎችን የሚናገር ሰው አንድ ችግር ያለውና ያንን በንግግር ለመሸፈን እየጣረ ነው ማለት ነው። መልካም ምስክርነት ያለው እውነተኛ ክርስቲያን ከሆንክ «አዎ» ወይም «አይደለም» ማለት ብቻ ይበቃሃል። ሰዎችም ያምኑሃል። ኢየሱስ ከዚህ ውጭ የሆኑ ነገሮች በሙሉ ክፉ ናቸው አለ።

መከራን ከምንቀበልባቸው ዓላማዎች አንዱ የባሕርይ መገንባት ነው። ኢዮብ እንደ እሳት በሆነው በዚህ ፈተና ውስጥ ካለፈ በኋላ ከበፊቱ የተሻለ ሰው መሆኑ ተረጋገጠ። (ያዕቆብ ይህንን ሂደት በምዕራፍ 1፡2-12 ላይ ይገልጥልናል።) ከአፋችን የሚወጡ ቃሎች የባሕሪይ መፈተኛዎች ከሆኑ መሐላ ደግሞ ገና መስተካከል ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ ያመለክተናል። ጴጥሮስ ጌታን እንደማያውቀው ሲምል፥ (ማቴ. 26፡71) ባሕርዩው ገና መለወጥ እንዳለበት ማረጋገጫ መስጠቱ ነበር።

ይህንን ክፍል በምትከልስበት ጊዜ ተግባራዊነቱን ትገነዘባለህ። ያዕቆብ በመከራ ውስጥ ታጋሽ እንድንሆን ሊያበረታታን ይፈልጋል። እንደ ገበሬ እግዚአብሔር የሚከብርበት ፍሬ ያለውን መንፈሳዊ ሰብል እንጠብቃለን። እንደ ነቢያት የእግዚአብሔርን እውነት ለሌሎች የምናካፍልበትን ዕድል እንጠብቃለን። እንደ ኢዮብ የእግዚአብሔር ልጆችን በማያስፈልግ ሁኔታ መከራ እንዲቀበሉ እንደማያደርግ በማወቅ ፍቅር የተሞላው ዓላማውን እንዲፈጽም ጌታን እንጠብቃለን። በተጨማሪ እንደ ኢዮብ ስለ ጌታ ግልጽ የሆነ ራዕይ ለማግኘት በመከራ ውስጥ በማለፍ እናድጋለን።

«የጌታ መምጣት ቅርብ ነውና ታገሡ!»

ያዕቆብ 5፡13-20

«ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር። ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል። እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበር፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፥ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።

«ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው፥ ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።»

እንጸልይ

የንግግር ስጦታ ለእግዚአብሔር ክብር ከተጠቀምንበት እጅግ ታላቅ በረከት ነው። እስካሁን ድረስ እንዳየነው ያዕቆብ ስለ አንደበት የሚለው እጅግ በርካታ ነገር ነበረው። በዚህም ምዕራፍ ይህንኑ ይቀጥላል። አንደበት መጠቀሚያ ሊሆን ስለሚችልበት ዝቅተኛ መንገዶች ይጠቅሳል፥ ማጉረምረም (5፡9)እና መማል (5፡12) ደግሞ አንደበት ጥቅም ላይ ሊውል ስለሚችልባቸው ከፍተኛ መንገዶች ይናገራል፤ የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ (5፡10) እና ጸሎትና እግዚአብሔርን ማመስገን ናቸው (5፡13)።

ጸሎት እጅግ ከፍተኛና የተቀደሰ መብት መሆኑ ያለ ጥርጥር እውነት ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጆች በነፃነትና በድፍረት ወደ ዙፋኑ በመምጣት የሚያስፈልገንን ነገር የመጠየቅ መብት ነው። ያዕቆብ በዚህ ክፍል ሰባት ጊዜ ያህል ጸሎትን ጠቅሷል። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ በሚያጋጥመው ችግር ይጸልያል። በሁኔታው ከማጉረምረም ፈንታ ስለ ጉዳዩ ለእግዚአብሔር በጸሎት ይናገራል። እግዚአብሔርም ጸሎቱን ይሰማዋል። «ነገሮችን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ» የበሰለ ክርስቲያን የሚለይበት መታወቂያ ነው።

በዚህ ክፍል ያዕቆብ እግዚአብሔር ጸሎትን የሚመልስባቸውን አራት ሁኔታዎች በመግለጽ እንድንጸልይ ያበረታታናል።

ለመከራ የሚደረግ ጸሎት (5፡13)

«ሥቃይ» የሚለው ቃል በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መከራን መቀበል ማለት ነው። «በመከራ ውስጥ» የሚለው ሐረግ ጥሩ ትርጉም ነው። ጳውሎስ ይህንን ቃል ለወንጌል ብሎ መከራ እየተቀበለ ሳለ የነበረበትን ሁኔታ ለመግለጥ ተጠቅሞበታል (2ኛ ጢሞ. 2፡9)። የእግዚአብሔር ሰዎች በሕይወት በሚመላለሱበት ጊዜ የኃጢአት ውጤት ወይም የእግዚአብሔር ቅጣት ያልሆኑ መከራዎችን ብዙ ጊዜ ይቀበላሉ።

እኛ ራሳችን በእንደዚህ ዓይነት ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ በምንገኝበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብን? ከእኛ በተሻለና ቀለል ባለ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ቅዱሳኖችን ማማትና መተቸት የለብንም (ያዕ. 5፡9)

ደግሞም ጌታን መውቀስ የለብንም። ያለንበትን ሁኔታ የምንረዳበትንና ለእግዚአብሔር ክብር የምናውልበትን ጥበብ ከእርሱ መጠየቅ አለብን (ያዕ. 1፡5)።

ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን ያስወግዳል። ደግሞም ጸሎት በመከራ ውስጥ የምንጸናበትንና የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ የምንፈጽምበትን ጸጋ ለማግኘት ይረዳናል። እግዚአብሔር መከራዎችን ወደ ድል ሊለውጣቸው ይችላል። «ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋ ይሰጣል ይላል» (ያዕ. 4፡6)። ጳውሎስ የነበረበት ሁኔታ እንዲለወጥ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔር ግን ድካሙን ወደ ኃይል በመለወጥ ጸጋን ሰጠው (2ኛ ቆሮ. 12፡7-10)። ጌታ በጌቴሴማኒ የሞት ጽዋ ከእርሱ ያልፍ ዘንድ ጸለየ፤ ጽዋው ግን አላለፈም። ይልቁኑ እግዚአብሔር አብ ወደ መስቀሉ እንዲሄድና ስለ ዓለም ኃጢአት እንዲሞት ብርታትን ሰጠው።

ያዕቆብ ሁሉም ክርስቲያን በአንድ ጊዜ ወደ ተመሳሳይ መከራ ወይም ችግር ውስጥ እንደማይገባ ያመለክታል፤ «ደስ ያለው ይዘምር» (5፡13)። እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚደርሱብንን ነገሮች በማመጣጠን መከራ የምንቀበልበትን ሰዓታት እንደሚሰጠን ሁሉ የምንዘምርበትንም ቀናት ይሰጠናል። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ክርስቲያን መከራን በሚቀበልበት ሰዓት እንኳ እንዴት እንደሚዘምር ያውቃል። (ችግሩ ካለፈ በኋላ ማንም ሰው መዘመር ይችላል)። እግዚአብሔር በሌሊት መዝሙርን መስጠት ይችላል (ኢዮብ 35፡10)። ለጳውሎስና ለሲላስ በፊልጵስዩስ እስር ቤት ውስጥ መከራን እየተቀበሉ በነበሩ ጊዜ ይህን አድርጎላቸዋል። «በመንፈቀ ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር» (የሐዋ. 16፡25)።

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጸሎትና መዝሙር በአምልኮ ጊዜ የሚደረጉ ዋና ዋና ነገሮች ነበሩ። ስለዚህ ለዘመናችን የአምልኮ ጊዜም እነዚህ ዋና ዋና ነገሮች መሆን አለባቸው። መዝሙራችን የውስጣዊ መንፈሳዊ ሕይወታችን መግለጫ መሆን አለበት። አማኞች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና በእውቀት የሚደረግ (1ኛ ቆሮ. 14፡15)፥ ለእነርሱ ትርጉም የማይሰጥ እንዲሁ ከአፋቸው የሚወጡ ቃላት ብቻ ሳይሆን ከልብ የወጣ መሆን አለበት (ኤፌ. 5፡19)። በመንፈስ ቅዱስም የተነቃቃ ሊሆንም ይገባል (ኤፌ. 5፡18)። ደግሞም የክርስቲያን የምስጋና መዝሙር በሰዎች የአእምሮ እውቀት ላይ ብቻ

ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት (ቆላ. 3፡16)። አንድ መዝሙር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

ለታመሙ የሚደረግ ጸሎት (5፡14-16)

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ የታመሙ ሰዎችን ለመፈወስ የሚያስችል አጠቃላይና ብቸኛ ደንብ መስጠቱ አይመስለኝም። በመጋቢነት በማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን እኔና ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች ለታመሙ ሰዎች ብዙ ጊዜ እንጸልያለን። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለዚያ ለታመመ ሰው ፈውስን ይሰጣል። በሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር ፈውስን አይሰጥም። በአንድ ሳምንት ልዩነት የተፈጸሙ ሁለት ታሪኮችን አስታውሳለሁ። እግዚአብሔር አንዷን ሴት ተአምራዊ በሆነ መንገድ ፈወሳት። ሌላኛዋ ሴት ግን ለቀዶ ጥገና ወደ ሆስፒታል መግባት ነበረባት። በመጨረሻም ጌታ ወደ ራሱ ወሰዳት።

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ የሚገልጸው ጉዳይ ልዩ ባሕርያት ምንድናቸው?

በሽተኛው የታመመው በኃጢአት ምክንያት ነው (5፡15፥ 16)፡- የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ «ያለማቋረጥ ኃጢአትን ካደረገ» ይላል። ይህ ደግሞ (ከ1ኛ ቆሮ. 11፡30) ጋር የሚመሳሰል ነው። «ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፥ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል።» ያዕቆብ የሚገልጸው ኃጢአትን ስላደረገና በእግዚአብሔር የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ምክንያት ስለታመመ የቤተ ክርስቲያን አባል ነው። ሕመምተኛው ወደ እነርሱ መሄድ ስለማይችል መንፈሳዊ መሪዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ ይጠይቃል። ከጉባኤ መካከል በእግዚአብሔር እየተቀጣ ላለ ማንኛውም ሰው መሪዎች የመጸለይ ኃላፊነት አለባቸው።

በሽተኛው የሠራቸውን ኃጢአቶች ይናዘዛል (5፡16)፡- በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በቤተ ክርስቲያን የሚወሰዱ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች ነበሯቸው። 1ኛ ቆሮ. 5 ለዚህ ጉዳይ በጣም ጥሩ ምሳሌ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች ኃጢአት የሠራውን አባል ከኃጢአቱ ንስሐ እስኪገባና መንገዱን እስኪያስተካክል ድረስ ከጉባኤያቸው እንዲያስወግዱት ነግሮአቸው ነበር። በያዕ. 5፡16 ላይ «እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ» የሚል ቃል ይገኛል። ያዕቆብ የተጠቀመው የግሪኩ

ቃል «ሃማርትያ» የሚል ሲሆን ትርጉሙም «ኃጢአት» ማለት ነው። በያዕ. 1፡15 ላይ በግልጽ ከተጠቀሰው ኃጢአት ጋር ተመሳሳይ ነው።

በሽተኛው የሚፈወሰው በእምነት በሚደረግ ጸሎት ነው (5፡15)፡- ፈውሱን የሚያመጣው ጸሎቱ እንጂ ዘይት መቀባቱ አይደለም። «ዘይት ቀብተው» ተብሎ የተተረጎመው ቃል መታሸት ከሚለው የግሪክ የሕክምና ቃል የመጣ ነው። ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፈውስ ከመጠበቅ ጋር በጊዜው የተገኘውን የፈውስ (የሕክምና) ዘዴ መጠቀምን መጠቆሙ እንደሆነ ነው። እግዚአብሔር በሕክምና መንገድ ወይም ያለሕክምና ሊፈውስ ይችላል፤ በሁለቱም ጊዜ ፈውሱን የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው።

ለመሆኑ በሽተኛውን የሚፈውሰው «የእምነት ጸሎት» ምንድን ነው? መልሱን በ1ኛ ዮሐ. 5፡14-15 ላይ እናገኘዋለን። «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንደሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን።» «የእምነት ጸሎት» የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ የሚደረግ ጸሎት ነው። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔርን አእምሮ ሊረዱና እንደ ፈቃዱ ሊጸልዩ ይገባል።

በእኔ ጉባኤ ውስጥ የሚገኙ በሽተኞችን በምጎበኝበት ጊዜ ለእነርሱ እንዴት እንደምጸልይ ሁልጊዜ አላውቅም። (ጳውሎስ ተመሳሳይ ችግር ነበረበት ሮሜ 8፡26ን አንብብ)። የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህንን ሰው መፈወስ ነውን? ወይስ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ራሱ ለመውሰድ ዐቅዶ ይሆን? የሚለውን ነገር ለመለየት ስለማንችል እንዲህ ብለን መጸለይ ይኖርብናል፡- «ፈቃድህ ከሆነ ልጅህን ፈውስ።» እግዚአብሔር በሽተኞችን ሁሉ ይፈውሳል። እግዚአብሔር ልጆቹ እንዲታመሙ ፈቃዱ አይደለም። የሚሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ተግባራዊ ልምምድን ይቃወማሉ። ከእግዚአብሔር ቃልም ሆነ ከመንፈሱ አንድን በሽተኛ ለመፈወስ ፈቃዱ እንደሆነ ካረጋገጥን በዚያን ጊዜ የእምነትን ጸሎት መጸለይ እንችላለን። ከጸልይንም በኋላ የእግዚአብሔርን ሥራ መጠበቅ እንችላለን።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጸልየው አንድ ሰው እንዳልሆነ ማስታወስ ተገቢ ነው። ጸሎቱን የሚያደርጉት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈለግ የሚጸልዩ መንፈሳዊ ሰዎች ማለትም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች

ናቸው። በዚህ ስፍራ ያዕቆብ ወደታመመው ሰው አንድ ፈዋሽ እንዲልኩ አላዘዛቸውም። ጉዳዩ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅ ያለ ነው።

በዚህ ስፍራ በቀላሉ ልናልፋቸው የማይገቡ አንዳንድ ተግባራዊ ትምህርቶች አሉ። የመጀመሪያው፥ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ወደ በሽታ ሊመራ መቻሉ ነው። ዳዊት ኃጢአቱን ለመደበቅ በሞከረ ጊዜ የተለማመደው ይህንኑ ነበር (መዝ. 32)። ሁለተኛው ነገር፥ ኃጢአት ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ይበክላል። ኃጢአት ሁልጊዜ የማደግና ሌሎችን የመበከል ባሕርይ ስላለው ብቻችንን ብቻ የምንሠራው አይደለም። ይህ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ኃጢአቱን መናዘዝ ነበረበት። ምክንያቱም ኃጢአትን ያደረገው በቤተ ክርስቲያን ላይ ነበር። ሦስተኛው ነገር፥ ኃጢአታችንን ከተናዘዝንና ከተውነው ሥጋዊና መንፈሳዊ ፈውስ ማግኘት መቻላችን ነው። «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» (ምሳሌ 28፡13)። ያዕቆብ ስለዚህ ጉዳይ የሰጠውን ምክር ቀጥተኛ ትርጉም ስንመለከተው «ኃጢአታችሁን እርስ በእርስ መናዘዝ ልምድ አድርጉት» የሚል ሆኖ እናገኘዋለን። ኃጢአትህን አትሸሽግ፤ ለመናዘዝም አትዘግይ።

ያዕቆብ የጻፈው በቅዱሳን መካከል ስለሚደረግ ኑዛዜ ነው። ኃጢአታችሁ ለሰባኪ ወይም ለካህን ተናዘዙ የሚል አሳብ ጨርሶ አልሰጠም። በመጀመሪያ፥ ኃጢአታችንን መናዘዝ ያለብን ለጌታ ነው (1ኛ ዮሐ. 1፡9)። በተጨማሪም ኃጢአታችን ጉዳት ላስከተለባቸው ሰዎች በሙሉ መናዘዝ ይጠበቅብናል። ከዚህ በላይ ኃጢአታችንን ለሌሎች እንናዘዝ ዘንድ ግን ጨርሶ አያስፈልግም። በግል የተሠራን ኃጢአት መናዘዝ የሚያስፈልገው በግል ሲሆን በሕዝብ ፊት የተሠራ ኃጢአትን ደግሞ በሕዝቡ ፊት ልንናዘዝ ያስፈልጋል። ክርስቲያኖች ኃጢአታቸውን ሁሉ በአደባባይ ማውጣታቸው ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት ኑዛዜ ከመጀመሪያው ኃጢአት የላቀ ጉዳት ሊያመጣ ይችላል።

ለሕዝቡ የሚደረግ ጸሎት (5፡17-18)

ያዕቆብ ኤልያስን በጸሎቱ እጅግ ኃይል ያደረገ «የጻድቅ ሰው» ምሳሌ አድርጎ አቅርቦታል። «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች» (ያዕ. 5፡16)።

የዚህን ታሪክ መሠረት በ1ኛ ነገሥት 17-18 ላይ እናገኘዋለን። እጅግ ክፉ የነበረው ንጉሥ አክአብና ንግሥቲቱ ኤልዛቤል የእስራኤልን ሕዝብ ከእግዚአብሔር አርቀው ወደ በኣል አምልኮ መርተውት ነበር። እግዚአብሔርም ሕዝቡን የሚያስፈልገውን ዝናብ በመከልከል ቀጣው (ዘዳ. 28፡12፥ 23 ተመልከት)። ለሦስት ዓመት ተኩል ሰማይ እንደ ነሐስ ሆነ፤ መሬትም ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ሰብሎች ሳትሰጥ ቀረች።

ኤልያስ የበኣል ነቢያትን በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ሙግት ገጠማቸው። ቀኑን በሙሉ እነዚህ የበኣል ነቢያት ወደ አምላካቸው ጮኹ፤ መልስ ግን አላገኙም። የምሽት መሥዋዕት በሚቀርብበት ሰዓት ኤልያስ መሠዊያውን እንደገና አደሰና መሥዋዕቱን አዘጋጀ። አንድ ጊዜ ብቻ ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ ከሰማይ የመጣች እሳት መሥዋዕቱን በላች። በዚህም እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን አረጋገጡ።

ሕዝቡ ግን ገና ዝናብ ያስፈልጋቸው ነበር። ኤልያስም ወደ ቀርሜሎስ ተራራ በመውጣት በጌታ ፊት በጸሎት ወደቀ። እየጸለየ እያለ ሰባት ጊዜ አገልጋዩን እየላከ የዝናብ መምጣት ምልክት እንዳለ ጠየቀው። በሰባተኛው ጊዜ አገልጋዩ ትንሽ ደመና አየ። ብዙም ሳይቆዩ ከፍተኛ ዝናብ ዘነበ፤ ሕዝቡም ከጥፋት ዳነ።

ዛሬስ የበረከት ዝናብ እንፈልጋለንን? በእርግጥ እንፈልጋለን።

«ኤልያስ የእግዚአብሔር ልዩ ነቢይ ስለነበር ነው» በማለት ልንከራከር እንችላለን። ስለዚህም እግዚአብሔር የእርሱን ጸሎት በአስደናቂ መንገድ እንደሚመልስ መጠበቅ ይቻላል።

ያዕቆብ እንዲህ በማለት ጠቅሶአል፡- «ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበር» (5፡17)። በእርግጥ ፍጹም አልነበረም፤ ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ካገኘው ድል በኋላ ወዲያውኑ ተስፋ ሲቆርጥ፥ ሲፈራና ሲሸሽ እንመለከተዋለን። ነገር ግን በእግዚአብሔር የታመነ በእርሱም የተደገፈ ጻድቅ ሰው ነበር። እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ የገባው ቃል ኪዳን የሚሠራው መንፈሳዊ ምርጦች ናቸው ብለን ለምናስባቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለልጆቹም ሁሉ ነው።

እግዚአብሔር ዝናብን እንደሚልክ ስለነገረው ኤልያስ በእምነት ጸለየ (1ኛ ነገ. 18፡1)። ሮበርት ላው ስለ ጸሎት እንዲህ ይላል፡- «ጸሎት የሰው ፈቃድ በሰማይ እንዲሆን የሚያደርግ አይደለም፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንዲሆን እንጂ።» የእግዚአብሔርን

ቃልና ጸሎትን መነጣጠል አይቻልም። ምክንያቱም በጸሎታችን ጊዜ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን ተስፋዎች የምናገኘው ከእግዚአብሔር ቃል ነውና።

ኤልያስ ባቀረበው ጸሎት ማመኑ ብቻ ሳይሆን ጸሎቱንም ያደረገው ያለ ማቋረጥና በትጋት ነበር። «አጥብቆ ጸለየ ... ሁለተኛም ጸለየ» (ያዕ. 5፡17-18)። ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ጸሎቱን ያለማቋረጥ ያደረገው አገልጋዩ ወደ እርሱ መጥቶ የሰውን እጅ የምታህል ደመና እንዳየ እስኪነግረው ድረስ ነበር። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠንን የተስፋ ቃሎች የማናገኘው ጸሎታችንን ስለምናቋርጥ ነው። በእርግጥ ጸሎታችንን የሚሰማው ደጋግመን በመጸለያችን አይደለም (ማቴ. 6፡7)። ነገር ግን ረብ በሌለው ድግግሞሽና በእውነተኛ የማያቋርጥ የእምነት ጸሎት መካከል ልዩነት አለ። ጌታ ኢየሱስ በጌቴሰማኒ የአትክልት ስፍራ ሦስት ጊዜ ጸለየ። ጳውሎስም የሥጋው መውጊያ እንዲወሰድለት ሦስት ጊዜ ጸለየ።

ኤልያስ በጸሎቱ ወሳኝና ትኩረት የሚሰጥ ነበር። «አጥብቆ ጸለየ» (ያዕ. 5፡17)። የግሪኩ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም «በጸሎት ውስጥ ሆኖ ጸለየ» የሚል መልእክት አለው። ብዙ ሰዎች በጸሎታቸው ውስጥ አይጸልዩም። ልባቸው በጸሎታቸው ጊዜ ከእነርሱ ጋር የለም። ስንፍና የሞላበት ሃይማኖታዊ ቃሎች ብቻ በቸልታ ይናገራሉ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ የጸሎት ስብሰባ አንድ አባል «በዓለም ዙሪያ ስላሉ ነገሮች» መጸለይ ጀመረ። በዚህ ስብሰባ ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ በንግግሩ ተሰላችቶ ነበር። ስለዚህ በመጨረሻ ሰውዬው «እግዚአብሔርን አንዳች ነገር ጠይቅ» በማለት ጮኸ። ስለ አንዳች ቁም ነገር መጸለይ ይህን ይመስላል።

ዛሬም ቢሆን በዓለም ላይ ከሚገኙ ኃይሎች ሁሉ ታላቁ ጸሎት ነው። «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች» (5፡16)። ታሪክ የሰው ልጅ ከሰው ጉልበት ወደ ፈረስ ጉልበት፥ ከዚያም ወደ ደግሚትና ሌሎች ትላልቅ የፈንጅ ኃይል፥ አሁን ደግሞ ወደ አቶሚክ ኃይል እንዴት እንደተሸጋገረ ያሳየናል።

ከአቶሚክ ኃይል ሁሉ የሚበልጠው ግን የጸሎት ኃይል ነው። ኤልያስ ስለ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም መለሰለት። ዛሬም ቢሆን ለሕዝባችን እግዚአብሔር እምነትንና መንፈሳዊ መነቃቃትን እንዲያመጣ በዚህም የበረከትን ዝናብን እንድንቀበል መጸለይ ያስፈልጋል። ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከተሰጡ

ኃላፊነቶች አንዱ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ለሚገኙ መሪዎች መጸለይ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡1-3)።

ከእውነት መንገድ የሳተን ሰው ለመመለስ የሚደረግ ጸሎት (5፡19-20)

ያዕቆብ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የጸሎትን ጉዳይ በሰም ባይጠቅስም አሳቡ ግን በዚያ እንዳለ ግልጽ ነው። ላዘኑና ለታመሙ ሰዎች የምንጸልይ ከሆነ ከእውነት ስተው ለሚቅበዘበዙ ወንድሞቻችን ደግሞ መጸለዩ አስፈላጊ ነው።

እነዚህ ቁጥሮች ከእውነት ስተው ወደ ኃጢአት ለገቡ አማኝ ወገኖቻችን ስለምንሰጠው የጸሎት አገልግሎት የሚናገሩ ናቸው። «መሳት» የሚለው ቃል ከእውነት ርቆ «መቅበዝበዝን» የሚያመለክት ሲሆን ድርጊቱም ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በመራቅ የሚፈጸም ነው። ለዚህ ጉዳይ ብሉይ ኪዳን የሚጠቀምበት ቃል «ወደ ኋላ መመለስ» የሚል ነው። እነዚህ ነገሮች ዛሬም በየአብያተ ክርስቲያኖቻችን ዘወትር የሚታዩ ነገሮች መሆናቸው የሚያሳዝን ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ አንድ ወንድማችን በስሕተቱ ሊወሰድ ይችላል (ገላ. 6፡17)። ይህ ዓይነቱ ኃጢአት ግን በዝግታና ቀስ በቀስ የሚፈጸም የመንፈሳዊ ማሽቆልቆል ውጤት ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ነገር በእርግጥ በጣም አደገኛ ነው። በደሉን ለሚፈጽመው ሰው አደገኛ የሚሆነው በጌታ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሊወሰድበት ስለሚችል ነው (ዕብ. 12)። ሌላው የሚያጋጥመው አደጋ «ሞት የሚገባው ኃጢአት» ሊፈጸም መቻሉ ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡16-17)። እግዚአብሔር ኃጢአትን ካደረጉ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት አንዳንዶቹን ወደ መንግሥተ ሰማያት እስከ መውሰድ ድረስ የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ቀጣቸው (1ኛ ቆሮ. 11፡30)።

ይህ ወደ ኋላ መመለስ ለቤተ ክርስቲያንም እንኳ አደገኛ ነው። ስቶ የሚቅበዘበዝ ኃጢአተኛ በሌሎች ሰዎችም ላይ ተፅዕኖ ሊያደርግና ወደ ስሕተት ሊመራ ይችላል። «አንድ ኃጢአተኛ ግን ብዙ መልካምን ያጠፋል» (መክብብ 9፡18)። መንፈሳዊ የሆኑ ክርስቲያኖች እርምጃ ሊወስዱና የተቀበዘበዘውን አማኝ ሊረዱ የሚገባው በዚህ ምክንያት ነው።

የዚህ ችግር መነሻ ሥሩ ከእውነት መሳት በሚለው ሐረግ ውስጥ ይገኛል (ያዕ. 5፡19)። እውነት ማለት የእግዚአብሔር ቃል ማለት እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። «ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ. 17፡17)። አንድ አማኝ በእውነት እስካልኖረ ድረስ ወደ ኋላ መገፋቱ አይቀርም። «ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል» (ዕብ. 2፡1)። ኢየሱስ፡- ጴጥሮስን ሰይጣን ሊፈትነው በደጅ እንዳለ በማመልከት አስጠነቀቀው፤ ጴጥሮስ ግን የኢየሱስን ቃል አላመነም። እንዲያውም ከጌታ ጋር ተከራከረ። መጸለይም ሲገባው አንቀላፋ፤ ስለዚህ ጌታን ሦስት ጊዜ መካዱ የሚያስደንቅ ነገር አይደለም።

የዚህ ከእውነት ስቶ የመንከራተት ኃጢአት ውጤት ሞት ሊሆን ይችላል (ያዕ. 5፡20)። በዚህ ስፍራ የምንመለከተው ኃጢአተኛ አማኝ እንጂ የማያምን ሰው አይደለም። በማያምን ሰው ከሚኖር ኃጢአት ይልቅ በክርስቲያን ሕይወት የሚገኝ ኃጢአት እጅግ ክፉ ነው። የማያምኑ ሰዎች ኃጢአትን እንደሚያደርጉ የሚጠበቅ ነው። እግዚአብሔር ግን ልጆቹ ለቃሉ እንዲታዘዙ ይፈልጋል።

አንድ አማኝ ወንድማችን ከእውነት ስቶ ሲንከራተት ብናየው ምን እናደርጋለን? በመጀመሪያ ልንጸልይለት ይገባል። ልንረዳውም ደግሞ ያስፈልጋል። ሊለወጥና እንደገና ወደ ትክክለኛው መንገድ ሊመለስ ያስፈልገዋል። አማኞች ለውጥ ያስፈልጋቸዋልን? አዎን ያስፈልጋቸዋል። ኢየሱስ ለጴጥሮስ እንዲህ ብሎት ነበር፥ «አንተ በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» (ሉቃስ 22፡32)።

የጠፉትን ሰዎች ወደ ጌታ ማምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። የዳኑትንም ሰዎች ለጌታ እንዲታዘዙ መምከርም አስፈላጊ ነው። አንድ ወንድማችን ቢበድለን ከእርሱ ጋር በግል ልንነጋገርና ለጉዳዩ መፍትሔ ልንፈልግ ያስፈልጋል። ከሰማን ወንድማችንን አዳንነው ወይም ማረክነው (ማቴ. 18፡15)። በያዕ. 4፡13 «እናተርፋለን» ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ናቸው። የዳኑትንም ሆነ የጠፉትን መማረክ አስፈላጊ ነው።

ስሕተትን የፈጸመ ክርስቲያንን ልንረዳ ከፈለግን ወደ እርሱ የሚመራን ዝንባሌ ፍቅር መሆን አለበት። «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና» (1ኛ ጴጥ. 4፡8)። ያዕቆብም ሆነ ጴጥሮስ ይህንን መመሪያ የተማሩት ከምሳሌ 10፡12 ላይ ነው። «ጥል ክርክርን ታስነሣለች ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች።»

ይህ ማለት ፍቅር ቆሻሻን ጠርጎ ከምንጣፍ ሥር የሚደብቅ ነው ማለት አይደለም። ፍቅር ባለበት ሁሉ እውነትም መኖር አለበት። ጳውሎስ በኤፌ. 4፡15 «እውነትን በፍቅር ተነጋገሩ» እንደሚለው እውነት ባለበት ሁሉ ኃጢአትን በታማኝነት መናዘዝ አለ። በዚህም ከእግዚአብሔር ዘንድ መንጻት ይገኛል። ፍቅር አንድ በደለኛን ከበደሉ ጋር እንዲጋፈጥና በትክክል መፍትሔ እንዲፈልግ ከማድረጉ ሌላ እነዚያ ኃጢአቶች አንድ ጊዜ ይቅር ከተባሉ በኋላ መታሰቢያ እንደሌላቸው ሆነው እንደሚረሱ ያረጋግጥልናል።

የእነዚህ ቁጥሮች መሠረታዊ ትርጉም ከላይ እንደተመለከትነው ቢሆንም ተግባራዊነታቸው ግን የጠፉትንም ሊያጠቃልል ይችላል። አንድ የሳተ ወንድም ግንኙነቱን ሊያድስ ካስፈለገው፥ አንድ የጠፋ ኃጢአተኛ ሰው ወደ አዳኙ መምጣት የበለጠ ያስፈልገዋል። አንድ የሳተ አማኝ ሕይወቱን የሚያጣ (በሥጋ ሞት የሚቀጣ) ቢሆንም እንኳ ቢያንስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይሄዳል። የጠፋ ኃጢአተኛ ግን ለዘለዓለም በገሃነም ይኮነናል።

«የጠፋውን መፈለግ» ነፍሳትን ለመማረክ የምንናገርበት እጅግ የተለመደ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕላዊ መግለጫ ነው። በሉቃስ 15 ኢየሱስ የጠፋውን በግ፥ የጠፋውን መክሊትና፥ የጠፋውን ልጅ ምሳሌ ተናገረ። ሁሉም ሊፈለጉና አስቀድመው ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ነፍሳት መማረክን ዓላ ከማጥመድም ጋር አወዳድሮታል (ማር. 1፡17)። ጴጥሮስ በግሉ በመንጠቆው በመጠቀም አንዳንድ ዓሣዎችን በየተራ ያጠምድ ነበር (ማቴ. 17፡24-27)፤ ከረዳቶቹም ጋር ደግሞ በመተባበርና መረቡን በመጠቀም በአንድ ጊዜ በርካታ ዓሣዎችንም ይይዝ ነበር። ለግልም ሆነ ለቡድን የወንጌል ሥራ መጽሐፍ ቅዱስ ስፍራ ሰጥቷል።

በምሳሌ 11፡30 እንደሚገኘው የወንጌል ሥራን፥ ከአደን ሥራ ጋር ያወዳድራል፤ «ነፍሳትን የሚሰበስብ እርሱ ጠቢብ ነው።» ኃጢአት የሚያጠምደው ለመግደል ነው (ያዕ. 1፡13-15)፤ እኛ ግን ነፍሳትን የምናጠምደው ሕይወትን እንዲያገኙ ነው።

በተጨማሪ ነፍሳትን ማራኪ የሰላም አምባሳደርም (መልእክተኛም) ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡20)። እግዚአብሔር እዚህ ዓለም ላይ ያወጀው ጦርነትን አይደለም፤ ሰላምን እንጂ! አንድ ቀን ግን ጦርነትን ያውጃል ፍርድም በሕዝብ ላይ ይሆናል።

ዘካርያስ 3፡2 ና ይሁዳ 23 ነፍሳትን ማራኪና ከእሳት የሚነጥቅ ሰው አድርገው ያቀርቡታል። ጆን ዊስሊ ዘካ. 3፡2ን ከራሱ ሕይወት ጋር አዛምዶታል። ልጅ በነበረ ጊዜ በእሳት ከተያያዘ ቤት ተነጥቆ ወጥቶ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ከፍርድ እሳት ነጥቆ ለማውጣት በፍቅር እራሳችንን አደጋ ላይ መጣል የሚያስፈልግበት ሁኔታ እንኳ ይኖራል።

ኢየሱስ ወንጌልን ዘር ከመዝራትና ከማጨድ ጋር አወዳድሮታል (ዮሐ. 4፡34-38)። ጳውሎስም መከርንም የመሰብሰቢያ ወራት አለ (1ኛ ቆሮ.3፡6-9)። ለሥራውም በርካታ ሰዎች ያስፈልጋሉ። «እኛም ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ሠራተኞቹ ነን» ብሎአል (1ኛ ቆሮ. 3፡9)። በጌታ የሥራ መስክ ውስጥ ውድድር ስለሌለ ዘሪውም፥ መከር ሰብሳቢውም ሽልማታቸውን አብረው ይቀበላሉ።

ይህ የያዕቆብ መልእክት ጥናታችንን ወደ ፍጻሜ ያመጣዋል። ትኩረቱ በመንፈሳዊ ብስለት ላይ ነበር። ልባችንን ለመመርመርና ምን ያህል የበሰልን መሆናችንን ለማየት ይህ ጥሩ ጊዜ ነው። ከዚህ በታች ሊረዷችሁ የሚችሉ ጥቂት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል።

1. በሕይወቴ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ ታጋሽ እየሆንኩ ነውን?
2. ከፈተና ጋር እጫወታለሁ? ወይስ ገና ከመጀመሪያው እቃወመዋለሁ?
3. የእግዚአብሔርን ቃል ዝም ብዬ አጠናዋለሁ ወይስ በመታዘዝ ደስታን አገኛለሁ?
4. ስለ ተለያዩ ሰዎችና ጉዳዮች የተሳሳተ ፍርድ ወይም ውሳኔ ላይ የሚያደርስ አስቀድሞ በአእምሮዬ የያዝኩት ነገር አለ?
5. አንደበቴን ለመግታት እችላለሁን?
6. ችግር ፈጣሪ ከመሆን ይልቅ ሰላም ፈጣሪ ነኝን? ከመንፈሳዊ ጥበብ እርዳትን ለማግኘት ሰዎች ወደ እኔ ይመጣሉን?
7. የእግዚአብሔር ወዳጅ ነኝ ወይስ የዚህ ዓለም ወዳጅ?
8. በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ሳላተኩር ዕቅድ አወጣለሁን?
9. በገንዘብ ጉዳይ ስስታም (ራስ ወዳድ) ነኝን? የሚፈለግብኝን ሁሉ ለመክፈል ታማኝ አይደለሁምን?
10. በአንዳንድ ችግሮች ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ በፍጥነት በጸሎት እደገፋለሁን?
11. ሌሎች ከእኔ የጸሎት ድጋፍ የሚፈልጉብኝ ዓይነት ሰው ነኝን?

12. እውነትን ለሳቱ ሰዎች ያለኝ ዝንባሌ ምንድን ነው? ስተቻቸውና ሳግቸው ነው የምገኘው ወይስ በፍቅር ስመልሳቸው?

በመንፈሳዊ ሕይወትህ ዕድሜህን እየቆጠርክ አታርጅ ወደ ብስለትም እደግ እንጂ!

አዲስ ኪዳንን መሠረት ያደረጉና
በዋረን ዌርዝቢ የተጻፉ

የ«ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ርኅሩኅ ሁን (የሉቃስ ወንጌል 1-13)
3. የበረታህ ሁን (የሉቃስ ወንጌል 14-24)
4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋርያት ሥራ 1-12)
5. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ 13-28)
6. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
7. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
8. አርነት መውጣት (ገላትያ)
9. ፍለጋ የሌለውን ባለጸግነት ውረስ (ኤፌሶን)
10. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
11. ፍጹም ሁን (ቈላስይስ)
12. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ)
13. ታማኝ ሁን (1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶና ፊልሞና)
14. በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ (ዕብራውያን)
15. በብስለት ማደግ (ያዕቆብ)
16. ንቃ! (2ኛ ጴጥሮስ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዮሐንስ፣ ይሁዳ)
17. ተስፋ አድርግ (1ኛ ጴጥሮስ)
18. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
19. ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)